የቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበራት

የፋይናንስ አገልግሎት አሰጣጥ

መመሪያ ቁጥር 982/2016 ዓ.ም

ጥር/2016 ዓ.ም

አዲስ አበባ

ስለ የቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበራት የፋይናንስ አገልግሎት አሰጣጥ የወጣ መመሪያ

በገንዘብ ቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበራት የማህበረሰቡን የፋይናንስ ንቃተ-ህሊና በማዳበር የቁጠባ ባህል በማሳደግ የአባላትን ፍላጎት መሰረት ያደረጉ የፋይናንስ አገልግሎቶች በቅርበት፣ በጥራት እና በተመጣጣኝ ዋጋ በማቅረብ የፋይናንስ ተደራሽነት ማሳደግ በማስፈለጉ፤

የቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበራት የአባላትን ፍላጎት መሠረት በማድረግ የተለያዩ የቁጠባ አገልግሎቶችን በመቅረጽና በማስፋፋት ተደራሽ እንዲሆኑ እና የሚሰጡ አገልግሎቶችን ጥራት፣ ቅልጥፍና እና ተመጣጣኝነት መቆጣጠር በማስፈለጉ፣

የቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበራት የሚሰጡት አገልግሎት የአባላትን ፍላጎት እና የአከባቢውን ሀብት መሠረት በማድረግ የተለያዩ የብድር አገልግሎቶችን በመቅረጽ በተመጣጣኝ ዋጋ፣ በቅርበትና በወቅቱ እንዲሰጡ ለማድረግ እና የአገልግሎቱን ውጤታማነት መረጋገጥ በማስፈለጉ፣

የቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበራት እና አባላት ከሚያከናውኑት ተግባር ጋር ተያይዞ ሊከሰት የሚችለውን የአደጋ ሲጋት በመቀነስ ውጤታማ እንዲሆኑ ለማድረግ የአነስተኛ ኢንሹራንስ አገልግሎት በመቅረጽ አገልግሎት መስጠት በማስፈለጉ፣

የማህበረሰቡን የፋይናንስ አገልግሎት ተደራሽነት ለማሳደግ እንዲቻል የአባላትን ፍላጎት መሠረት በማድረግ የወለድ አልባ የፋይናንስ አገልግሎት በመቅረጽና በማስፋፋት አገልግሎቱን ለሚፈልገው የሕብረተሰብ ክፍል ተደራሽ ማድረግ በማስፈለጉ፣

በኅብረት ሥራ ማህበራት አዋጅ ቁጥር 985/2009 አንቀጽ 76(3) መሠረት በማድረግ የኢትዮጵያ ኅብረት ሥራ ኮሚሽን ይህን መመሪያ አውጥቷል፡፡

<u>ክፍል አንድ</u>

<u>ጠቅላላ</u>

1) አጭር ርዕስ

ይህ መመሪያ **"የቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበራት የፋይናንስ አገልግሎት አሰጣጥ መመሪያ ቁጥር** 982/ 2016" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2) ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ የተለየ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ መመሪያ ውስጥ፡

1. **"የቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበር"** ማለት አነስተኛ የፋይናንስ አገልግሎት ለመስጠት በኅብርት ሰራ ማህበራት አዋጅ ቁጥር 985/2009 መሰረት የተቋቋሙ መሠረታዊ የቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበር፣ የቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበራት ዩኒዬኖችና የቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበራት ፌዴሬሽኖች ማለት ነው፡፡
2. **"መደበኛ ቁጠባ"** ማለት ማንኛውም የቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበር በወሰነው ዝቅተኛ የገንዘብ መጠን እና የጊዜ ገደብ መሰረት በማድረግ አባሉ በግል ስምምነት የወሰነውን የቁጠባ መጠን በገንዘብ ወይም በዓይነት በተከታታይነት የሚሰበሰብ ቁጠባ ነው፡፡
3. **"የፍላጎት ቁጠባ**" ማለት ማንኛውም የቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበር ከመደበኛው ቁጠባ በተጨማሪ በአባላት ፍላጎት የሚሰበሰብ የቁጠባ አይነት ነው፡፡
4. "**የልጆች ቁጠባ**" ማለት የቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበራት አባላት በሆኑ ወላጆች ወይም አሳዳጊዎች አማካኝነት ዕድሜያቸው ከ18 ዓመት በታች ለሆኑ ህፃናት የሚቆጥቡላቸው የቁጠባ ዓይነት ነው፡፡
5. **"የዓይነት ቁጠባ"** ማለት በማንኛውም የቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበር ከአባላት ሰብል ምርት እና እንስሳት በዓይነት ሰብስቦ ወደ ጥሬ ገንዘብ በመቀየር የሚቆጠብ የቁጠባ ዓይነት ነው፡፡
6. **"የዕጣና ቁጠባ ምጥጥን"** ማለት የቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበር በወሰነው መሠረት ዕጣን እና መደበኛ ቁጠባ በማመጣጠን ከአባላት ገንዘብ የሚሰበስብበት አሰራር ነው፡፡

7. **"የአነስተኛ ንግድ ብድር"** ማለት የተበዳሪውን ፍላጎት መሠረት በማድረግ ለአነስተኛ ሱቅ ንግድ፣ ለጉሊት ንግድ፣ ለትራንስፖርት አገልግሎት፣ ለአነስተኛ የግብርና ምርት ማቀነባበር፣ ለቱሪዝም እና ተያያዥ ተግባራትን ለማከናወን የሚሰጥ የብድር ዓይነት፡፡

8. **"ለማህበራዊ ጉዳዮች የሚሰጥ ብድር"** ማለት የተበዳሪውን ፍላጎት መሠረት በማድረግ ለሕክምና፣ ለትምህርት፣ የቤት ቁሳቁሶችን ለማሟላት፣ ለሰርግ እና ሌሎች ገቢ ለማያመነጩ ተግባራት የሚሰጥ የብድር ዓይነት ነው፡፡

9. **"የቡድን ብድር"** ማለት ሁለትና ከዚያ በላይ የሆኑ ግለሰብ አባላት በፍላጎታቸው በተናጠል ተበድረው በመካከላቸው በሚኖረው ስምምነት በአንድ የንግድ ስራ ዕቅድ በጋራ እንዲሰሩ የሚሰጥ የብድር ዓይነት ነው፡፡

10. **"የገጠር መሬት ይዞታ ማረጋገጫ ሰርተፍኬት"** ማለት የገጠር መሬት የመጠቀም መብትን ለማረጋገጥ አግባብ ባለው አካል የተሰጠ ሰነድ ነው፡፡

11. **"ማዕከላዊ የፋይናንስ አገልግሎት"** ማለት የቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበራት ዩኒዬኖች እና ፌዴሬሽኖች የአባላትን የፋይናንስ አገልግሎት ፍላጎት መሠረት በማድረግ የሚሰጡት የቁጠባ፣ የብድር እና የአነስተኛ ኢንሹራንስ የፋይናንስ አገልግሎት ነው፡፡

12. **"አረቦን"** ማለት አነስተኛ ኢንሹራንስ አገልግሎትን ለመስጠት እንዲቻል ከተበዳሪ የሚሰበሰብ ገንዘብ ነው፡፡

13. **"ኮሚሽን"** ማለት የኢንሹራንስ አገልግሎት ሰጪው ወኪሎቹ በሰበሰቡት አረቦን ልክ በስምምነታቸው መሠረት በመቶኛ የሚከፈል የአገልግሎት ክፍያ ነው፡፡

14. **"ወለድ አልባ የፋይናንስ አገልግሎት"** ማለት የእስልምና ህግን (ሸሪዓን) መሠረት በማድረግ የሚሠራ በዋናነት ወለድ መቀበልና መክፈልን በጥብቅ የሚከለክል የቁጠባና ብድር የኅብረት ሥራ ማህበራት የፋይናንስ አገልግሎት ማለት ነው፡፡

15. **"በመስኮት የሚሰጥ ወለድ አልባ የፋይናንስ አገልግሎት"** ማለት ወለድ አልባ የፋይናንስ አገልግሎት እና ወለድ የሚታሰብበት የፋይናንስ አገልግሎት ጎን ለጎን የሚሰጥበት የቁጠባና ብድር የኅብረት ሥራ ማህበር አሰራር ስርዓት ማለት ነው፡፡

16. **"ሸሪዓ"** ማለት የእስልምና እምነት ተከታዮች የሚመሩበት ህግና ድንጋጌ ማለት ነው፡፡

17. **"ዋዲዓ የድ ደማን ቁጠባ"** ማለት የቁጠባና ብድር ኅበረት ስራ ማህበራት ከአባላት የሚሰበስቡት ወለድ አልባ መደበኛ ቁጠባ ነው፡፡

18. **"የሸሪዓ ግብይት ስርዓት"** ማለት የሸሪዓ ስርዓትን የተከተለ የቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማኅበራት የግዥና የሽያጭ አፈፃፀም ስርዓት ማለት ነው፡፡
19. **"የሙራባሃ ብድር"** ማለት ዕቃ ገዝቶ በተገዛበት ዋጋ ላይ ወጪን እና የትርፍ ህዳግን ጨምሮ በዱቤ መልክ ለመሸጥ በውል ስምምነት የሚሰጥ የወለድ አልባ ብድር አገልግሎት ነው፡፡
20. **"የትርፍ ህዳግ"** ማለት ዕቃ በተገዛበት ዋጋ ላይ የሚጨመር የትርፍ መጠን ማለት ነው፡፡
21. **"የሰለም ብድር"** ማለት የግብርና ምርቶችን በቅድመ ክፍያ ከአባላት ለመግዛት በውል ስምምነት የሚሰጥ የወለድ አልባ የብድር አገልግሎት ነው፡፡
22. **"የኢጃራ ብድር"** ማለት ንብረትን ለማከራየት እና የተገዛበትን ዋጋ ለማስከፈል በውል ስምምነት የሚሰጥ የወለድ አልባ የብድር አገልግሎት ነው፡፡
23. **"የሙሻረካ ብድር" ማለት የወለድ አልባ የብድር አገልግሎት ዓይነት ሲሆን** በመሰረታዊ የቁጠባና ብድር የኅብረት ሥራ ማህበር እና በገንዘብ ቁጠባና ብድር የኅብረት ሥራ ማህበራት ዩኒዬን መካከል ወይም በመሰረታዊ የቁጠባና ብድር የኅብረት ሥራ ማህበር እና በግለሰብ አባላት መካከል ትርፍን እና ኪሳራን ለመጋራት የሚደረግ የሽርክና ስምምነት ማለት ነው፡፡
24. **"ተካፉል ተአውኒ"** ማለት መተባበርን እና መረዳዳትን መሰረት በማድረግ በገንዘብና ቁጠባ ብድር ኅብረት ሰረ ማህበር የሚሰጥ አነስተኛ የኢንሹራንስ አገልግሎት ነው፡፡
25. **"ተባሩ"** ማለት የተካፉል ተአዉኒ አገልግሎት ተጠቃሚ የሆኑ አባላት እንደ ስጦታ ወይም ልገሳ በማሰብ የሚያዋጡት የገንዘብ መጠን ነው፡፡
26. "**የአሰራር ስርዓት"** ማለት የቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበራት የፋይናንስ አገልግሎት አሰጣጣቸውን በውስጥ አሰራር ለመምራት እንዲያስችላቸው በራሳቸው አዘጋጅተውና አስፀድቀው የሚጠቀሙበት ሰነድ ነው፡፡
27. በዚህ መመሪያ ውስጥ ማንኛውም በወንድ ጾታ የተገለጸው ሴትንም ያካትታል፡፡

3) የተፈፃሚነት ወሰን

ይህ መመሪያ በመላው ሀገሪቱ በኅብረት ሥራ ማህበራት አዋጅ ቁጥር 985/2009 መሰረት በተለያየ ደረጃ በተደራጁ የቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበራት ላይ ሁሉ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

ክፍል ሁለት

የቁጠባና ዕጣ አስተዳደርና አጠቃቀም ስርዓት

4) የቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበር የቁጠባ አሰባሰብ፣ አስተዳደርና አጠቃቀም

1. ማንኛውም መሠረታዊ የቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበር መደበኛ ቁጠባ መሰብሰብ አለበት፣
2. የቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበር የመደበኛ ቁጠባ አሰባሰብ እና አስተዳደር ስርዓት ከዚህ በታች እንደሚከተለው ተፈጻሚ ይሆናል
   ሀ. የቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበር ከአባላት የሚሰበስው መደበኛ ቁጠባ መጠን እና ጊዜው በመተዳደሪያ ደንብ ወይም በቁጠባ አሰራር ስርዓት መወሰን አለበት፤
   ለ. ማንኛውም የቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበር፤ ከአባሉ የሚሰበስበው የመደበኛ ቁጠባ መጠን አባሉ በማመልከቻ በጠየቀው መሠረት መሆን አለበት፡፡
   ሐ. ማንኛውም የቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበር በአባሉ በሚቀርብለት ጥያቄ መሰረት ከመደበኛ ቁጠባ መጠን ከፍ ወይም ዝቅ እንዲያደርጉ በየስድስት ወሩ ሊፈቅድላቸው ይችላል፤
   መ. ማንኛውም የቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበር አባላት በመደበኛ ቁጠባ ለመቁጠብ በወሰኑት የገንዘብ መጠን መሰረት ከየፍላጎት ቁጠባ ተቀናሽ በማድረግ ወደ መደበኛ ቁጠባ እንዲዘዋወርለት አባሉ ሲጠይቅ ሊያዛውር ይችላል፤
   ሠ. ማንኛውም የቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበር ለሚሰበስበው ገንዘብ ህጋዊ የገቢ ደረሰኝ መስጠት እና በግል ደብተርና ቋት መመዝገብ አለበት፤
3. በዚህ አንቀፅ ንኡስ አንቀፅ 1(ለ እና ሐ) ላይ የተደነገገው የመደበኛ ቁጠባ መጠን በኀብረት ሥራ ማህበሩ መተዳደሪያ ደንብ ወይም የቁጠባ አሰራር ስርዓት ላይ ከተቀመጠው ዝቅተኛ የመደበኛ ቁጠባ መጠን በታች ሊሆን አይችልም፡፡
4. የመኖሪያ አካባቢን መሰረት አድርጎ የተቋቋመ ማንኛውም መሠረታዊ የቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበር የሚሰበስበው ቁጠባ የአባሉን ገቢ መሰረት በማድረግ በገንዘብ መጠን መሆን አለበት፡፡
5. ተቋምን መሰረት አድርጎ የሚቋቋም ማንኛውም መሠረታዊ የቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበር ቁጠባ የሚሰበስበው ቁጠባ ከአባሉ ደመወዝ በመቶኛ ተቀንሶ አባሉ የወሰነው መጠን መሆን አለበት፡፡

6. ማንኛውም መሰረታዊ የቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበር በቁጠባ አሰራር ስርዓት ላይ በተቀመጠው መሠረት መደበኛ ቁጠባ በአይነት ሊሰበስብ ይችላል፤
7. የቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበራት ዩኒየን እና ፌዴሬሽን የመደበኛ ቁጠባ ከአባላቱ መሰብሰብ ይችላሉ፤
8. የቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበር የመደበኛ ቁጠባ አጠቃቀም ከዚህ በታች እንደሚከተለው ተፈጻሚ ይሆናል
   ሀ. የማንኛውም የቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበር አባላት መደበኛ ቁጠባቸውን ለብድር ዋስትና መጠቀም ይችላሉ፤
   ለ) ማንኛውም የቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበር ለአንድ አባል የሚሰጠውን የብድር መጠንን ለመወሰን የአባሉን መደበኛ ቁጠባ መጠቀም ይችላል ፤
   ሐ. ማንኛውም የቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበር አባል ከኅብረት ሥራ ማህበሩ እስካለቀቀ ድረስ የመደበኛ ቁጠባውን ወጪ ማድረግ አይችልም፣
9. በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 8 (ሐ) ላይ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ አባሉ የተወሰነ መደበኛ ቁጠባ ወጪ አድርጎ መጠቀም እንዲችል የኅብረት ሥራ ማህበሩ ካመነበት በመተዳደሪያ ደንቡ ወይም በቁጠባ አሰራር ስርዓት ላይ ባስቀመጠው አሰራር መሠረት ወጪ ማድረግ ይችላል።

5) **የቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበር የፍላጎት ቁጠባ አሰባሰብና አስተዳደር**

1. ማንኛውም የቁጠባና ብድር ኅብረት ስራ ማህበር የፍላጎት ቁጠባ መሰብሰብ ይችላል
2. አዲስ የተቀረጸ የፍላጎት የቁጠባ አገልግሎት ሥራ ላይ ከመዋሉ በፊት አግባብ ላለው ባለስልጣን ቀርቦ መመዝገብ አለባቸው፤
3. የፍላጎት ቁጠባ አገልግሎት መሰጠት ከመጀመሩ በፊት አሰራሩ በኅብረት ሥራ ማህበሩ የቁጠባ የአሰራር ስርዓት ማሟላት አለበት፤
4. የኅብረት ሥራ ማህበሩ የቁጠባ ገንዘብ መሰብሰቢያና ወጪ ማድረጊያ እለታዊ አገልግሎት ሊሰጥ ይችላል።
5. ማንኛውም የቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበር የፍላጎት ቁጠባን ለብድር አገልግሎት መጠቀም ይችላል።

6. ማንኛውም የቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበር የሰበሰበዉን የፍላጎት ቁጠባ በብድር ዋስትናነት ካልተያዘ በማንኛዉም ጊዜ ወጪ እንዲያደረግ መፍቀድ አለበት፡፡

6) **የቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበር የዓይነት ቁጠባ አሰባሰብ እና አስተዳደር**

1. ማንኛውም የቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበር የዓይነት ቁጠባ ሊሰበስብ ይችላል፡፡
2. ማንኛውም የቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበር የሰበሰበውን የዓይነት ቁጠባ ወደ ቁጠባ ዞሮ ለመመዝገብ ወደ ጥሬ ገንዘብ እንዲቀየር ማድረግ አለበት፡፡
3. ማንኛውም የቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበር የሚሰበሰበው የአይነት ቁጠባ ዝርዝር አፈጻጸም በመተዳደሪያ ደንብና በቁጠባ የአሠራር ስርዓት መሠረት የሚተገበር ይሆናል፤

7) **የቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበር ማዕከላዊ የፋይናንስ አገልግሎት አተገባበር እና አስተዳደር**

1. የማዕከላዊ የፋይናንስ አገልግሎት መስጠት የሚችሉት የቁጠባና ብድር የኅብረት ሥራ ማህበራት ዩኒዬኖች እና ፌዴሬሽኖች ብቻ ይሆናሉ፤
2. ማንኛውም የቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበራት ዩኒዬን እና ፌዴሬሽን ማዕከላዊ የፋይናንስ አገልግሎት ለመስጠት የሚያስችል የአሰራር ስርዓት አዘጋጅቶና አጸድቆ መጠቀም አለበት፡፡
3. ማንኛውም የቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበራት ዩኒዬን እና ፌዴሬሽን የአባላትን የፋይናንስ አገልግሎት ፍላጎትን መሰረት በማድረግ አዳዲስ ማዕከላዊ የፋይናንስ አገልግሎት በመቅረጽ አገልግሎት መስጠት አለበት፡፡
4. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 መሰረት የተቀረፀው ማዕከላዊ የፋይናንስ አገልግሎት በስራ ላይ የሚውለው አግባብ ባለው ባለስልጣን ከተመዘገበ በኂላ ይሆናል፤

8) **የቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበር የቁጠባ ወለድ ስሌት አሰራር**

1. ማንኛውም የቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበር የቁጠባ ወለድ መጠን በብሔራዊ ባንክ ከተቀመጠው የወለድ መጠን በታች መሆን የለበትም፤
2. ማንኛውም የቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበር የራሱን የቁጠባ ወለድ መጠን በጠቅላላ ጉባኤ አፀድቆ ተግባራዊ ማድረግ አለበት፤

3. ማንኛውም የቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበር የቁጠባ ወለድ ስሌት አባሉ የቆጠበውን የገንዘብ መጠን እና የቆይታ ጊዜ መሠረት ማድረግ አለበት፤
4. ማንኛውም የቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበር የቁጠባ ወለድ ማስላት የሚጀምረው ቁጠባው ከተሰበሰበበት ቀን ጀምሮ መሆን አለበት፡፡
5. የቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበር የፍላጎት የቁጠባ አገልግሎት የወለድ ምጣኔ እንደየ ቁጠባ አይነቱ ሊለያይ ይችላል፤
6. ማንኛውም የቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበር የፍላጎት ቁጠባን ለማበረታታት የሚከፈለውን የወለድ መጠን በአካባቢው ያሉ የፋይናንስ ተቋማት ከሚከፍሉት የወለድ መጠን ጋር ተወዳዳሪ ማድረግ ይችላል፡፡

9) **በገንዘብ ቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበር የቁጠባ አሰባሰብ ሂደት የአባላት መብት እና ግዴታ**

1. ማንኛውም የቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበር አባል በቁጠባ አሰባሰብ ላይ የሚከተሉት መብቶች ይኖሩታል
   ሀ. በኅብረት ሥራ ማህበሩ መተዳደሪ ደንብ ወይም የቁጠባ የአሰራር ስርዓት መሰረት ቁጠባን ለብድር ዋስትና የማስያዝ፤
   ለ. አባሉ የሚቆጥበውን የመደበኛ ቁጠባ የገንዘብ መጠን በተቀመጠው የጊዜ ገደብ ውስጥ ከፍ ወይም ዝቅ የማድረግ፤
   ሐ. ቁጠባን በተመለከተ መረጃ ጠይቆ የማግኘት እንዲሁም ቅሬታ ሲኖር የማቅረብና መልስ የማግኘት፤
   መ. በኅብረት ሥራ ማህበሩ የወለድ አሰላል መሰረት ለቆጠበው ገንዘብ ተመጣጣኝና ወቅቱን የጠበቀ ወለድ የማግኘት፤
   ሠ. በኅብረት ሥራ ማህበሩ መተዳደሪያ ደንብ ወይም የቁጠባ መመሪያ መሰረት የፍላጎት ቁጠባን ወጪ የማድረግ፣
2. ማንኛውም የቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበር አባል በቁጠባ አሰባሰብ ላይ የሚከተሉት ግዴታዎች አሉበት፡-
   ሀ. መደበኛ ቁጠባን በተከታታይ የመቆጠብ ፤
   ለ. መደበኛ ቁጠባንና ዕጣን በየጊዜው አመጣጥኖ የመቆጠብ
   ሐ. አባሉ በመደበኛነት የሚቆጥበውን የገንዘብ መጠን ከፍ ወይም ዝቅ ለማድረግ ሲፈልግ በማመልከቻ ማሳወቅ አለበት፤

መ. በኅብረት ሥራ ማህበሩ መተዳደሪያ ደንብ መሰረት ያሉ ከቁጠባ ጋር የተያያዙ መመሪያዎችን የማክበርና ተግባራዊ የማድረግ፤

10) **የቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበር በቁጠባ አሰባሰብ ላይ የሚኖረው ተግባርና ኃላፊነት**

1. አዋጆችንና መመሪያዎችን በማይጣረስ መንገድ ቁጠባን በተመለከተ የአሰራር ሥርዓት ማዘጋጀት፣
2. በመተዳደሪያ ደንብ ወይም በቁጠባ የአሰራር ስርዓት መሰረት አባላት ማንኛውንም አይነት የቁጠባ አገልግሎት ማግኘት ሲፈልጉ ፈጣን ምላሽ መስጠት አለበት፣
3. የቁጠባ አገልግሎትን በተመለከተ ለአባላት መረጃ መስጠት አለበት
4. ቁጠባን በተመለከተ ከአባላት ለሚቀርቡ ቅሬታዎች ፈጣን ምላሽ መስጠት አለበት፣
5. አዳዲስ የቁጠባ አገልግሎቶችን ማስተዋወቅና ማስፋፋት አለበት፤

11) **የቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበር ዕጣ አሰባሰብ፣ አስተዳደርና አጠቃቀም**

1. የዕጣና ቁጠባ ምጥጥን የሚተገብሩ የቁጠባና ብድርኅብረት ሥራ ማህበራት ዕጣ ማወጅ ይችላሉ፤
2. በዚህ አንቀፅ ንኡስ አንቀጽ 1 ላይ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበር የካፒታል እጥረት በሚያጋጥመው ወቅት ተጨማሪ ዕጣ በማወጅ ሊሸጥ ይችላል፤
3. የቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበር ለአባላት የሸጠው ዕጣ አባሉ ሲለቅ ዕጣውን መልሶ ለገበያ ማቅረብ አለበት፣
4. ማንኛውም መሠረታዊ የቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበር የቁጠባና የዕጣ ምጥጥን መተግበር አለበት፤
5. ማንኛውም የቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበር ዩኒየን እና ፌዴሬሽን የቁጠባና የዕጣ ምጥጥን መተግበር ይችላል፤
6. በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 1 እና 2 ላይ የተደነገገው የዕጣና ቁጠባ ምጥጥን የሚቀመጠው ዝቅተኛው 1:7 ሲሆን ከፍተኛው 1:3 መብለጥ የለበትም፤
7. የቁጠባና ብድር የኅብረት ሥራ ማህበር የዕጣና ቁጠባ ምጥጥን አሰራር በመተዳደሪያ ደንብ ወይም በቁጠባ አሰራር ስርዓት ላይ ማስቀመጥ አለበት፣

8. ማንኛውም የቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበር የሚሰበስበው የአባላት እጣ፤ የመደበኛ ቁጠባ ደህንነት የሚጠብቅ በመሆኑ ገቢ በማያስገኙና የረጅም ጊዜ ኢንቨስትመንት ላይ ማዋል የለበትም፣

<u>ክፍል ሶስት</u>

<u>የብድር አስተዳደርና አተገባበር ስርዓት</u>

12) የቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበራት የብድር አሰራር ስርዓት መዘርጋት

1. ማንኛውም የቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበር የሚሰጠውን ብድር ለማስተዳደር፣ ለመቆጣጠርና ለማስመለስ እንዲችል ይህንን መመሪያ እና መተዳደሪያ ደንቡን መሠረት በማድረግ የራሱን የብድር የአሰራር ስርዓት በማዘጋጀትና በማጸደቅ አገልግሎት መስጠት አለበት፡፡
2. የቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበራት የሚያዘጋጁት የብድር የአሰራር ስርዓት ይዘት በዋናነት ከዚህ በታች የተዘረዘሩ ነጥቦችን ማካተት አለበት፡-
   ሀ) የቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበሩን ሥምና አድራሻ፤
   ለ) የሚሰጠው የብድር አገልግሎት ዓይነትና ዓላማ፤
   ሐ) የብድር አገልግሎት ላይ ውሳኔ የሚሰጡ አካላት ስልጣንና ተግባር፤
   መ) ለአንድ አባል የሚሰጥ የብድር ጣሪያ፤
   ሠ) የተጨማሪ ብድር አጠያየቅ፤
   ረ) የብድር መመለሻ ጊዜ
   ሰ) የብድር አመላለስ ሂደት፤
   ሸ) የብድር መመለሻ ጊዜ ስለማራዘም፤
   ቀ) የብድር ወለድ መጠን፤
   በ) የብድር ማመልከቻ አቀራረብ እና አወሳሰን፤
   ተ) የብድር ዋስትና ዓይነትና ማጠን፣
   ቸ) የብድር ውል አሰራርና አፈጻጸም፣
   ነ) ብድር ለማግኘት የሚያስፈልጉ መስፈርቶች እና ብድር የሚያስከለክሉ ጉዳዮች፣
   ኘ) የብድር አሰራር ስርዓት ስለማሻሻል፤

3. በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 2 ላይ የተጠቀሱትን መስፈርቶች ተከትሎ የተዘጋጀ የብድር አሰራር ስርዓት በኅብረት ሥራ ማህበሩ ጠቅላላ ጉባዔ ሳይጸድቅ እና አግባብ ላለው ባለስልጣን ቀርቦ ሳይመዘገብ ሥራ ላይ መዋል የለበትም፡፡

13) የቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበራት የብድር ኮሚቴ አደረጃጀት፣ ተግባርና ኃላፊነት

1. ማንኛውም የቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበር በጠቅላላ ጉባዔ የተመረጠ የብድር ኮሚቴ ሊኖረው ይችላል፡፡
2. የብድር ኮሚቴ አባላት ቁጥር ከ3-5 ሲሆን ሰብሳቢ፣ ፀሐፊና አባላት ይኖሩታል፡፡
3. በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 1 ላይ የተጠቀሰው የብድር ኮሚቴ እንደተጠበቀ ሆኖ የቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበሩ የብድር ባለሙያ ወይም ባለሙያዎችን ቀጥሮ ሊያሰራ ይችላል፡፡
4. በብድር ውሳኔ አሰጣጥ ላይ የብድር ኮሚቴ እና የብድር ባለሙያዎች ሊኖራቸው የሚገባው ተግባርና ኃላፊነት በብድር አሰራር ስርዓት መደንገግ ይኖርበታል፡፡
5. ለብድር ኮሚቴ የሚመረጥ ማንኛውም አባል የሚከተሉት መስፈርቶችን ማሟላት አለበት፡-
   ሀ) በአባላት ዘንድ ተቀባይነት ያለው፣ ቅን፣ ታማኝ፣ ታታሪ፣ ተቆርቃሪና የማያወላውል፣
   ለ) የቀረበለትን የብድር ጥያቄ መርምሮ ውሳኔ ለመስጠት የተሻለ ችሎታ ያለው፣
   ሐ) የኅብረት ሥራ ማህበሩን የብድር አሰራር ስርዓት፣ መተዳደሪ ደንብ እና ሌሎች አሰራሮችን በአግባቡ የተረዳ ፣
   መ) ከሰዎች ጋር ተግባብቶ መስራት የሚችል፣
6. የቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበራት የብድር ኮሚቴ የሚከተሉት ተግባርና ኃላፊነት ይኖረዋል፡-
   ሀ) ከተበዳሪዎች የሚቀርብ የብድር ጥያቄ በገንዘብ ቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበሩ የብድር የአሰራር ስርዓትና መተዳደሪያ ደንብ መሠረት መሆኑን ያረጋግጣል፣
   ለ) የብድር ዕቅድ ያዘጋጃል ወይም እንዲዘጋጅ ያደርጋል፣
   ሐ) ለብድር ጥያቄ የሚያስፈልጉ ቅጹ-ቅጾች ያዘጋጃል ወይም እንዲዘጋጅ ያደርጋል፣
   መ) ተበዳሪዎች የሚሞሉት የብድር ማመልከቻ ቅጽና የውል ሰነድ አሞላል ላይ ድጋፍ ያደርጋል፤ የብድር አጠቃቀም ላይ ያማክራል፣

ሠ) ከተበዳሪዎች የቀረቡትን የብድር ጥያቄዎች መቀበልና በቅደም ተከተል ውሳኔ መስጠት ወይም እንዲሰጥ ማድረግ፣

ረ) ተበዳሪዎች የጠየቁትን የብድር ጥያቄ ለመመለስ በቂ ገንዘብ መኖሩን ያረጋግጣል፣

ሰ) ተበዳሪዎች ለጠየቁት ብድር በቂና ሕጋዊ ዋስትና መቅረቡን ያረጋግጣል፣

ሸ) ለብድር ጥያቄው መሟላት የሚገባቸው ሰነዶች መሟላታቸውን እና ትክክለኛነት ያረጋግጣል፣

ቀ) ተበዳሪዎች ለብድር ዋስትናነት ያቀረቧቸውን ሰነዶችና መረጃዎች በአግባቡ ይይዛል ወይም እንዲያዝ ያደርጋል፣

በ) በኅብረት ሥራ ማህበሩ መተዳደሪያ ደንብ ወይም ውስጠ ደንብ ውስጥ በተቀመጠው ጊዜ ስብሰባዎችን በማድረግ ውሳኔዎችን ያስተላልፋል፣

ተ) በሥራ ላይ ያለውን የብድር አሰራር ስርዓት በመገምገምና የታዩ ክፍተቶችን በመለየት እንዲሻሻል ያደርጋል፣

ቸ) ተበዳሪዎች የተበደሩትን ብድር ለታቀደው ተግባር እያዋሉ ስለመሆናቸው ይከታተላል ወይም ክትትል እንዲደረግበት ያደርጋል፣

ነ) የመመለሻ ጊዜው የደረሰ ብድር በአግባቡ እየተመለሰ መሆኑን ይከታተላል፣

ኘ) ተጨማሪ ብድር እና የብድር መመለሻ ማራዘሚያ ጊዜ የተጠየቀባቸውን ማመልከቻዎች መርምሮ ውሳኔ ይሰጣል ወይም እንዲሰጥበት ያደርጋል፣

አ) የብድር ሪፖርትና መረጃ ለሚመለከተው አካል ያቀርባል፣

14) የቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበራት የብድር ዓይነትና የቆይታ ጊዜ

1. ማንኛውም የቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበር የአባላትን ፍላጎት መሠረት ያደረገ ብድር ማቅረብ አለበት፡፡
2. የቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበራት ለአባላት የሚያቀርቡት የብድር ዓይነት በዋናነት ገቢ በሚያመነጩ ዘርፎች ላይ ሆኖ በሚከተሉት የሥራ መስኮች ላይ ትኩረት ማድረግ አለበት፡-

ሀ) በግብርና ዘርፍ፣

ለ) በአነስተኛ ንግድ ማስፋፋት፣

ሐ) በቤቶች ግንባታና እድሳት፣

መ) በትራንስፖርት ዘርፍ፣

ሠ) በማህበራዊ ጉዳዮች፣

ረ) በአነስተኛ የግብርና ምርት ማቀነባበር ተግባር፣

3. በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 2 ላይ የተጠቀሰው እንደተጠበቀ ሆኖ ገቢ ለማያመነጩ ተግባራት የሚውል ብድር መጠን አነስተኛ መሆን አለበት፡፡
4. በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 2 ላይ ለተጠቀሱ የሥራ ዘርፎች የሚውል የብድር መጠን በመቶኛ በብድር አሰራር ስርዓት ውስጥ በመደንገግ ተግባራዊ ማድረግ አለባቸው፡፡
5. የቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበራት የአባላትን ፍላጎት፣ የአከባቢውን ሃብትና የሥራ ዘርፍ መሠረት በማድረግ የተለያዩ የብድር አገልግሎት ዓይነቶችን በመቅረጽ አገልግሎት መስጠት አለበት፡፡
6. በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 5 ላይ በተደነገገው መሠረት አዲስ የተቀረጸ የብድር አገልግሎት ሥራ ላይ የሚውለው አግባብ ላለው ባለሥልጣን ቀርቦና ተገምግሞ ከጸደቀና ከተመዘገበ በኋላ ይሆናል፡፡
7. የቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበራት የሚሰጡት ብድር የቆይታ ጊዜ ከዚህ እንደሚከተለው የተለያየ ሊሆን ይችላል፡-

   ሀ) በአንድ ዓመት ውስጥ የሚመለስ የአጭር ጊዜ ብድር፣

   ለ) ከአንድ ዓመት እስከ አምስት ዓመት ጊዜ ውስጥ የሚመለስ የመካከለኛ ጊዜ ብድር፣

   ሐ) ከአምስት ዓመት እስከ አሥር ዓመት ጊዜ ውስጥ የሚመለስ የረጅም ጊዜ ብድር፣

8. በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 7 (ሐ) ላይ የተጠቀሰው የብድር የቆይታ ጊዜ እንደተጠበቀ ሆኖ የኅብረት ሥራ ማህበሩ ካመነበት ከተቀመጠው የረጅም ጊዜ ቆይታ በላይ ብድር መስጠት ይችላል፡፡
9. የቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበራት ከ10 ዓመታት በላይ የቆይታ ጊዜ የሚሰጡት የብድር መጠን አጠቃላይ ከሚሰጠው ብድር ውስጥ መጠኑ አነስተኛ መሆን አለበት፡፡
10. የአባላትን ፍትሃዊ ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ ሲባል የቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበራት የሚሰጡት የብድር የቆይታ ጊዜ በአብዛኛው የአጭር እና የመካከለኛ ጊዜ መሆን አለበት፡፡

15) የቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበራት የብድር አገልግሎት ተጠቃሚዎች እና መሟላት የሚገባቸው ቅድመ-ሁኔታዎች

1. የቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበራት ብድር ማቅረብ ያለባቸው በቅድሚያ ለግለሰብ አባላት እና ለአባል ኅብረት ሥራ ማህበራት መሆን አለበት፡፡
2. የቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበራት የአባላትን የብድር ፍላጎት አሟልቶ የሚተርፍ ገንዘብ ሲኖር የኅብረት ሥራ ማህበራት መርህን በመከተል ፍላጎት ላላቸው ለሌሎች ኅብረት ሥራ ማህበራት ብድር ሊሰጡ ይችላል፡፡
3. በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 1 እና 2 ላይ የተጠቀሱ ጉዳዮች እንደተጠበቁ ሆነው፤ የቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበር ከመንግስት እና ከሌሎች መንግስታዊ ያልሆኑ አካላት የሚያገኘውን ተዘዋዋሪ ፈንድ በሚደረግ የጋራ ስምምነት መሠረት አባል ላልሆነ ግለሰብ የብድር አገልግሎት መስጠት ይችላል፡፡
4. የቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበራት የሚያቀርቡት ብድር የተናጠል ብድር መሆን አለበት፡፡
5. በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 4 ላይ የተጠቀሰው እንደተጠበቀ ሆኖ አዋጭነቱ በጥናት ሲረጋገጥ የቡድን ብድር ሊሰጥ ይችላል፡፡
6. በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 5 ላይ የተገለጸው የቡድን ብድር አሰጣጥና ክትትል፤ በኅብረት ሥራ ማህበሩ የብድር አሰራር ስርዓት ውስጥ በተቀመጠው መሠረት ተግባራዊ የሚደረግ ይሆናል፡፡
7. ማንኛውም ከገንዘብ ቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበር የብድር አገልግሎት ማግኘት የሚፈልግ ግለሰብ አባል ወይም አባል ኅብረት ሥራ ማህበር የሚከተሉትን መስፈርቶች ማሟላት አለበት፡-
   ሀ) የኅብረት ሥራ ማህበሩ አባል የሆነ እና ብድር ለማግኘት በኅብረት ሥራ ማህበሩ የብድር አሰራር ስርዓት ውስጥ የተጠቀሰውን የቆይታ ጊዜ የሚያሟላ፣
   ለ) የቆጠበው ገንዘብ ለመበደር ካቀረበው የገንዘብ መጠን ጋር ሲነጻጸር በኅብረት ሥራ ማህበሩ ብድር አሰራር ስርዓት ላይ ከተቀመጠው ጋር የተጣጣመ ሲሆን፣
   ሐ) ለብድሩ በቂ ዋስትና ማቅረብ ሲችል፣
   መ) ያቀረበው የንግድ ሥራ ዕቅድ ተቀባይነት ሲያገኝ፣
   ሠ) በኅብረት ሥራ ማህበሩ ብድር አሰራር ስርዓት ላይ የተጠቀሱ ሌሎች መስፈርቶችን ሲያሟላ፣

8. የብድር ኮሚቴ ወይም የብድር ባለሙያ የቀረበለትን የብድር ጥያቄ ከመወሰኑ በፊት የሚከተሉትን መስፈርቶች በአግባቡ መፈተሽ ይኖርበታል፡-

ሀ) ብድር ጠያቂው ብድሩን የፈለገበት የሥራ መስክ ላይ ያለው አቅም እና ብድር የመጠቀም ልምድ፣

ለ) ብድር ጠያቂው ያለው ንብረት ከጠየቀው ብድር ጋር መጣጣም፣

ሐ) ብድር ጠያቂው ለጠየቀው ብድር ያቀረበው ዋስትና ከብድሩ ጋር የተጣጣመ ስለመሆኑ

መ) ብድሩን ለታለመለት ተግባር ለማዋል ያለው ነባራዊ ሁኔታ፣

9. ማንኛውም ተበዳሪ ከተበደረበት ተግባር ውጭ ገንዘቡን በሌላ ጉዳይ ላይ ማዋል አይችልም፡፡

10. በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 9 ላይ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ተበዳሪው የተበደረበት ተግባር አዋጭ አለመሆኑን ለኅብረት ሥራ ማህበሩ ሲያመለክት ችግሩን በመገምገም ተበዳሪው በሌላ አዋጭ ተግባር ላይ እንዲያውል ሊፈቅድለት ይችላል፡፡

16) የቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበር የብድር ምንጮች፣ የፋይናንስ ግብይት ትስስር እና ተዘዋዋሪ ፈንድ አጠቃቀምና አስተዳደር፣

1. የቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበር የብድር ምንጮች የሚከተሉት ሊሆኑ ይችላሉ፡-

ሀ) ከአባላት የተሰበሰበ ቁጠባ፣

ለ) የተመለሰ ብድር፣

ሐ) ከሌሎች ተቋማት እና ግለሰቦች በጊዜ ገደብ ቁጠባ የተገኘ ገንዘብ፣

መ) የቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበራት እርስ በርስ ወይም ከሌሎች ኅብረት ሥራ ማህበራት ወይም ከፋይናንስ ተቋማት ወይም ከአበዳሪ ተቋማት ጋር በሚያደርጉት የፋይናንስ ግብይት ትስስር የተገኘ ገንዘብ፣

ሠ) መንግስታዊ ወይም መንግስታዊ ካልሆኑ ተቋማት የተሰጠ ተዘዋዋሪ እና በስጦታ የተገኘ ፈንድ፣

2. በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 1(ሀ) ላይ የተገለጸው ቁጠባ ለብድር መዋል ያለበት ከአጠቃላይ ሃብት ጋር ሲነጻጸር ከ70-80 ከመቶ ሊበልጥ አይችልም፡፡

3. በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 1(መ) ላይ የተገለጸው የፋይናንስ ግብይት ትስስር ተግባራዊ የሚሆነው አስፈላጊነቱ ተጠንቶ አዋጭነቱ ሲረጋገጥ ብቻ ይሆናል፡፡

4. በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 1(ሠ) ላይ የተጠቀሰው ተዘዋዋሪ ፈንድ ተግባራዊ የሚሆነው በሁለቱም ተቋማት ስምምነት መሠረት በማድረግ አሰራር ከተዘረጋለት በኋላ ይሆናል፡፡

17) የቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበራት የብድር ጥያቄ አቀራረብ፣ ግምገማ፣ የብድር ውል ስምምነት፣ የብድር ጣሪያ እና ብድር ስለመልቀቅ፡-

1. የብድር ጥያቄ ማመልከቻ ይዘት የሚከተሉትን ያካተተ መሆን አለበት፡-
   ሀ) የተበዳሪው ሙሉ ሥም እና አድራሻ፣
   ለ) የብድር መጠን፣
   ሐ) ብድሩ የተፈለገበት የሥራ ዘርፍ፣
   መ) የብድር ዘመንና የክፍያ ጊዜ፣
   ሠ) ተበዳሪው ያለው ቁጠባና ዕጣ መጠን፣
   ረ) የሚያቀርበው ዋስትና ዓይነትና መጠን በብር፣
   ሰ) አመልካቹ በገንዘብ ቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበሩ ውስጥ ለሌላ አካል ዋስ ሆኖ ከሆነ የብድሩን መጠን እና ብድሩ ያለበት ሁኔታ፣
   ሸ) አመልካቹ ከገንዘብ ቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበሩ ብድር ወስዶ ያልመለሰው ካለ የብድር መጠኑን እና ያለበትን ሁኔታ፣
2. በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 1 ላይ የተቀመጠው እንደተጠበቀ ሆኖ በገቢ ማስገኛ ተግባራት ላይ ለሚጠየቅ ብድር ተበዳሪው ከብድር ማመልከቻ ጋር የንግድ ሥራ ዕቅድ አያይዞ ማቅረብ አለበት፡፡
3. የብድር ኮሚቴ ወይም ባለሙያ የብድር አመልካቹ ያቀረበውን ማመልከቻ ለማረጋገጥ የሚከተሉትን ተግባራት ሊያከናውን ይችላል፡-
   ሀ) አመልካቹ የጠየቀውን ብድር ለታለመለት ተግባር ለማዋል ያለው ተነሳሽነት ለማረጋገጥ ቃለ መጠይቅ ማድረግ፣
   ለ) አመልካቹ ከዚህ በፊት ብድር ወስዶ ተጠቅሞበት መመለሱን እና ብድር የመጠቀም የኋላ ታሪኩን ማጥናት፣
   ሐ) አመልካቹ የጠየቀው ብድር በራሱ ፍላጎት የቀረበ እና ማመልከቻው ትክክለኛ መሆኑን ማረጋገጥ፣
   መ) ለብድር ጥያቄው በቂ ማስረጃዎች መቅረባቸውን ማረጋገጥ፣
   ሠ) በአመልካቹ የቀረበው ዋስትና ትክክለኛነትና ሕጋዊነት ማረጋጋጥ፣

4. በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 3 የተደረገው ቃለ መጠይቅ መረጃ ተጠናቅሮና ተፈርሞ ከአመልካቹ የብድር ማመልከቻ ጋር ተያይዞ በአባሪነት መቀመጥ አለበት፡፡
5. የብድር ኮሚቴው ወይም ባለሙያው የቀረበለትን የብድር ጥያቄ መርምሮ በገንዘብ ቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበሩ የብድር አሰራር ስርዓት ላይ በተቀመጠው የጊዜ ገደብ ውስጥ ውሳኔ መስጠት አለበት፡፡
6. ብድር ጠያቂው መሠረታዊ ወይም ዩኒዩን ኅብረት ሥራ ማህበር ከሆነ የሚያቀርበው ማመልከቻ ከዚህ በታች የተዘረዘሩ ሰነዶችን ማካተት አለበት፡-
   ሀ) የፋይናንስ አቋማቸውን የሚገልጽ ዝርዝር ሪፖርት፣
   ለ) ብድሩ የሚውልበት ዝርዝር ተግባር፣
   ሐ) የሚሰማሩበት ተግባር ለግብይት እና ኢንቨስትሜንት ከሆነ የንግድ ሥራ ዕቅድ ማቅረብ፣
   መ) የጠቅላላ ጉባዔ ወይም በብድር ላይ ስልጣን የተሰጠው አካል የውሳኔ ቃለ-ጉባዔ ማቅረብ፤
7. የቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበር ብድር ስርጭት ተፈፃሚ የሚሆነው በመተዳደሪያ ደንብና በብድር አሰራር ስርዓት መሰረት ይሆናል፡፡
8. ማንኛውም ብድር የሚሰጠው ኃላፊነት ባለው የብድር ባለሙያ ወይም በብድር ኮሚቴ ወይም በስራ አስኪያጅ ወይም በሥራ አመራር ኮሚቴ ወይም በቦርድ ተገምግሞ ሲፀድቅ ብቻ ነው፡፡
9. በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 8 ላይ የተቀመጠው፤ በብድር ባለሙያ ወይም በብድር ኮሚቴ ወይም በስራ አስኪያጅ ወይም በሥራ አመራር ወይም ቦርድ የሚፀድቅ የብድር ገንዘብ መጠን ገደብ በብድር አሰራር ስርዓት በተገለፀው መሠረት ተግባራዊ የሚደረግ ይሆናል፡፡
10. ማንኛውም የቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበር የሚሰጠውን የብድር ጣሪያ በማጥናትና በብድር አሰራር ስርዓት በመወሰን ተግባራዊ መደረግ አለበት፡፡
11. በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 10 ላይ የተጠቀሰው የብድር ጣሪያ ውሳኔ የሚከተሉት ጉዳዮች ላይ ማተኮር አለበት፡-
   ሀ) የተሰበሰበ መደበኛ ቁጠባ እና ዕጣ መጠን፣
   ለ) ከውጭ ሊገኝ የሚችለው ተጨማሪ የፋይናንስ ምንጭ፣
   ሐ) የአባላት የብድር ፍላጎት እና የመመለስ አቅም፣

መ) ብድር ለመውሰድ የሚስፈልገውን ዋስትና የማግኘት ሁኔታ፣

12. ማንኛውም የቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበር ለሚሰጠው ብድር የውል ስምምነት ሰነድ በማዘጋጀት መጠቀም አለበት፡፡

13. በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 12 ላይ የተጠቀሰው የብድር ውል የሚከተሉትን ነጥቦችን ማካተት ይችላል፡-

ሀ) የተበዳሪው እና የዋሱ ሙሉ ሥምና አድራሻ፣

ለ) የተያዘው የብድር ዋስትና ዓይነትና መጠን፣

ሐ) የብድሩ ዓላማ፣ የሚመለስበት ጊዜ እና የወለድ መጠን፣

መ) የኅብረት ሥራ ማህበሩና የተበዳሪው መብትና ግዴታ፣

ሠ) ተበዳሪው ኃላፊነቱን በአግባቡ መወጣት ካልቻለ ሊወሰዱ የሚችሉ እርምጃዎች፣

ረ) የቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበሩን በመወከል ብድሩን የሚያጸድቅ አካል ፊርማ፣

ሰ) ተበዳሪው እና ዋሱ ውሉን በማየት በፊርማቸው የሚያረጋግጡበት ቦታ፣

14. የብድር ውሉ ከተበዳሪው ማመልከቻ እና ከብድር ኮሚቴ ውሳኔ ጋር ተያይዞ በገንዘብ ቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበሩ ጽሕፈት ቤት ውስጥ በጥንቃቄ መቀመጥ አለበት፡፡

15. የብድር ገንዘብ ለተበዳሪው የሚለቀቀው ከዚህ በታች በተቀመጡ አሰራር መሠረት መሆን አለበት፡-

ሀ) ማንኛውም የቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበር ተበዳሪው አስፈላጊውን የብድር መስፈርቶች ካሟላ በብድር አሰራር ስርዓት መሠረት በተቀመጠው ጊዜ ውስጥ ብድሩን መልቀቅ አለበት፣

ለ) ማንኛውም የቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበር ለተበዳሪው የሚከፍለው ብድር በጥሬ ገንዘብ ወይም ከሂሳብ ቁጥር ወደ ሂሳብ ቁጥር ወይም በቼክ ሊሆን ይችላል፡፡

ሐ) በብድር አሰራር ስርዓት ውስጥ በተደነገገው መሠረት ተበዳሪው የተፈቀደለትን ገንዘብ አሳማኝ ባለሆነ ምክንያት በተባለው ቀን ካልወሰደ ብድሩ ሊሰረዝ ይችላል፡፡

18) በገንዘብ ቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበር ተጨማሪ ብድር ስለመፍቀድ

1. ተበዳሪው የተበደረውን ብድር የመመለሻ ጊዜው ሳይጠናቀቅና ከፍሎ ሳይጨርስ ተጨማሪ ብድር ከጠየቀ ሊፈቀድለት ይችላል፡፡

2. በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 1 ላይ የተጠቀሰው ተጨማሪ ብድር ተግባራዊ የሚሆነው አዲስ ብድር የጠየቁ አባላት ከተስተናገዱ በኂላ መሆን አለበት፡፡
3. በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 1 ላይ የተገለጸው ተጨማሪ ብድር የሚፈቀደው የሚከተሉትን ሁኔታዎች መሠረት በማድረግ መሆን አለበት፡-
   ሀ) የኅብረት ሥራ ማህበሩ በቂ ፋይናንስ ያለው መሆኑ ሲረጋገጥ፣
   ለ) ተበዳሪው ያቀረበው የተጨማሪ ብድር ጥያቄ ተገቢ መሆኑ ሲረጋገጥ፣
   ሐ) የተበዳሪው የመክፈል አቅም አስተማማኝ ሲሆን፣
   መ) የተበዳሪው የቀድሞ የብድር አመላለስ ሁኔታ የተሻለ መሆኑ ከታመነበት፣
   ሠ) ለተጨማሪ ብድር በቂ ዋስ ማቅረብ የሚችል ከሆነ፣
   ረ) ተበዳሪው ለተጨማሪው ብድር የውል ስምምነት መፈጸም ሲችል፣
4. ተበዳሪው ተጨማሪ ብድር ማግኘት የሚችለው መጀመሪያ ከተበደረው ብድር ውስጥ 50 በመቶ እና ከዚያ በላይ መመለሱ ሲረጋገጥ መሆን አለበት፡፡
5. በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 1 ላይ የተቀመጠው ተጨማሪ ብድር እንደተጠበቀ ሆኖ በሁለት ዙር የተሰጠውን ብድር መልሶ ሳይጨርስ ለሦስተኛ ዙር ብድር መስጠት አይቻልም፡፡
6. ተጨማሪ የሚሰጥ የብድር መጠን በዝርዝር ጥናት ላይ ተመስርቶ በብድር አሰራር ስርዓት ውስጥ በማካተት ተግባራዊ መደረግ አለበት፡፡

19) የቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበር ብድር ለመስጠት የሚያዝ የብድር ዋስትና ዓይነትና መጠን

1. ማንኛውም የቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበር ያለዋስትና ብድር መስጠት አይችልም፡፡
2. ማንኛውም የቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበር ብድር ከመስጠቱ በፊት ተበዳሪው ተመጣጣኝ እና ሕጋዊ ዋስትና ማቅረቡን ማረጋገጥ አለበት፡፡
3. ተበዳሪው የጠየቀው ብድር ከቆጠበው መደበኛ ቁጠባ በላይ ካልሆነ መደበኛ ቁጠባው እንደ ዋስትና ሊያገለግለው ይችላል፡፡
4. በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 3 ላይ የተገለጸው እንደተጠበቀ ሆኖ ከዚህ በታች የተዘረዘሩት ለብድር ዋስትና ሊውሉ ይችላሉ፡-
   ሀ) የኅብረት ሥራ ማህበሩ አባል የሆነ እና መደበኛ ቁጠባ ያለው፣
   ለ) ተበዳሪው በራሱ የሚያቀርባቸው ሕጋዊ ተንቀሳቃሽና ቋሚ ንብረቶች፣

ሐ) የተበዳሪው ወይም የሌሎች ሰዎች ሕጋዊ የገጠር መሬት ይዞታ ማረጋገጫ ሰርተፍኬት፣

መ) በተበዳሪው በሕጋዊነት የተያዙ ቋሚ ተክሎች እና እንስሳት፣

ሠ) የማህበሩ አባል ያልሆነ ሰው ሕጋዊ ተንቀሳቃሽና ቋሚ ንብረት፣

ረ) የተበዳሪው አባል ቋሚ ደመወዝ፣

ሰ) የኅብረት ሥራ ማኅበሩ አባል ወይም አባል ያልሆነ ቋሚ ደመወዝ፣

ሸ) በአቻ ኅብረት ሥራ ማህበር አባል የሆነ ግለሰብ ለሌላ አቻ ኅብረት ሥራ ማህበር አባል ዋስ መሆን፤

ቀ) መንግስታዊና መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች የዋስትና ፈንድ፤

በ) የአክሲዮን ሰርትፊኬት፤

5. በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 4 (ሀ-ረ) ላይ የተዘረዘሩት የዋስትና አይነቶችን ተግባራዊ ለማድረግ የቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበሩ ዝርዝር ጥናት በማድረግ በራሱ ተጨባጭ ሁኔታ ሊተገበሩ የሚችሉትን በመለየት በብድር አሰራር ስርዓት በማካተት መተግባር አለበት፡፡
6. ማንኛውም የቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበር የአባሉን የፍላጎት ቁጠባ በአሰራር ስርዓት ውስጥ በማካተት በዋስተናነት መያዝ ይችላል፡፡
7. በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 6 ላይ በተደነገገው አግባብ የፍላጎት ቁጠባን በዋስትናነት መያዝ የሚቻለው ከዚህ በታች የተዘረዘሩ ጉዳዮችን መሠረት በማድረግ መሆን አለበት፡-

    ሀ) ብድሩ ሳይመለስ ተበዳሪው የፍላጎት ቁጠባውን ማውጣት እንደማይችል ከተስማማ፣

    ለ) ተበዳሪው የሚወስደው ብድር የሌሎች አባላትን መብት የማይነካ መሆኑ ሲረጋገጥ፣

    ሐ) የተበዳሪው የፍላጎት ቁጠባ ለብድር ዋስትናነት ለመጠቀም በብድር አሰራር ስርዓት ውስጥ የተቀመጠውን የጊዜ ገደብ የሚያሟላ ከሆነ፤

8. ተበዳሪው የሚያቀርባቸው ዋሶች ባለትዳር ከሆኑ ባልና ሚስት በብድር ውል ላይ መፈረም አለባቸው፡፡
9. ማንኛውም ተንቀሳቃሽና ቋሚ ንብረት በዋስትናነት ማስያዝ የሚቻለው ከዕዳና እገዳ ነጻ መሆኑ ከሚመለከተው አካል ማረጋገጫ ሲሰጥ ብቻ ነው፡፡

10. ከላይ በንዑስ አንቀፅ 9 የተጠቀሰው ንብረት ለብድር ዋስትናነት ሲያዝ በሚመለከተው አካል ተመዝግቦ ማረጋገጫው ለአበዳሪው የቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበር መድረስ አለበት፡፡
11. የብድር ዋስትና ሊቀየር የሚችለው ለቀሪው ዕዳ ተተኪ ዋስትና ሲገኝ እና ውል እንደ አዲስ ሲፈረም ብቻ መሆን አለበት ፡፡

20) **የቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበራት የብድር ወለድ አሰላል እና አተገባበር**

1. ማንኛውም የቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበር ወለድ ለሚያስከፍል የብድር አገልግሎት ወለድ ማስከፈል አለበት፡፡
2. ማንኛውም የቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበር ለሚሰጠው የብድር አገልግሎት የሚያስከፍለው የወለድ መጠን እንደ አገልግሎቱ ዓይነት ሊለያይ ይችላል፡፡
3. በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 2 ላይ የተጠቀሰው የብድር ወለድ መጠን እንደ ኅብረት ሥራ ማህበሩ ተጨባጭ ሁኔታ በሚደረግ ዝርዝር ጥናት መሰረት በብድር አሰራር ስርዓት ውስጥ ተካቶ ተግባራዊ መድረግ አለበት፡፡
4. የማንኛውም ገንዘብ ቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበር የብድር ወለድ ምጣኔ አወሳሰን የሚከተሉትን ታሳቢ ማድረግ አለበት፡-
   ሀ) ለብድር የሚውለው ገንዘብ የሚያስከትለው ወጭ፣
   ለ) የኅብረት ሥራ ማህበሩ አስተዳደራዊ ወጭ፣
   ሐ) መመለስ ለማይችሉ ብድሮች ማካካሻ ተቀማጭ፣
   መ) የኅብረት ሥራ ማህበሩ የትርፍ ህዳግ፣
   ሠ) ወቅታዊ አማካይ የግሽበት መጠን፣
5. በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 4 (ሀ-ሠ) ላይ የተደነገጉ ጉዳዮች እንደተጠበቁ ሆነው ማንኛውም የቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበር የፋይናንስ ገበያውን ፍላጎትና አቅርቦት በማየት የወለድ ምጣኔውን ሊከልስ ይችላል፡፡
6. የብድር ወለድ መታሰብ የሚጀመረው ተበዳሪው የብድር ውል ፈጽሞ ገንዘቡን ወጭ አድርጎ ከወሰደበት ቀን ጀምሮ ይሆናል፡፡
7. ማንኛውም የቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበር የብድር ወለድ ክለሳ በሚያደርግበት ጊዜ ለአባላት በቃል ወይም በፅሁፍ ማሳወቅ አለበት፡፡
8. የማንኛውም የቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበር የብድር ወለድ የሚያሰላው የተቀናናሽ የብድር ወለድ አሰራርን ተከትሎ መሆን አለበት፡፡

9. በተቀመጠው የብድር አሰራር ስርዓት መሠረት ተበዳሪው የብድር ወለድን ከዋናው ብድር ጋር አብሮ መክፈል ይችላል፡፡
10. ተበዳሪው ብድሩን በወቅቱ ካልከፈለ የብድር የወለድ ወለድ እና ቅጣት ታስቦ የሚከፍል ሆኖ ለተበዳሪው እና ለዋሱ በጊዜው መገለፅ አለበት፡፡

21) **የቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበር የብድር አመላለስ እና የመመለሻ ጊዜ ስለማራዘም**

1. ማንኛውም የቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበር የሰጠውን ብድር ዓይነትና የመመለሻ ጊዜ ታሳቢ በማድረግ ተበዳሪው ብድሩን መመለስ የሚጀምርበት ጊዜ በብድር አሰራር ስርዓት ውስጥ በማካተት መተግበር አለበት፡፡
2. ማንኛውም የቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበር ለተበዳሪዎች የሰጠውን ብድር በውሉ መሠረት መመለስ በሚገባው ቀን ማስመለስ አለበት፡፡
3. በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 1 ላይ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ተበዳሪው የወሰደውን ብድር የመመለሻ ጊዜው ሳይደርስ ሊመልስ ይችላል፣
4. ማንኛውም ተበዳሪ የተበደረውን ብድር ዋናውን፣ ወለዱን እና ሌሎች ወጭዎችን በመጨመር በውሉ መሠረት የመክፈል ግዴታ አለበት፡፡
5. ተበዳሪው በገባው ውል መሠረት ብድሩን መመለስ ካልቻለ የብድር ኮሚቴ ወይም የብድር ባለሙያ ተበዳሪውን በማነጋገር ብድሩን እንዲመልስ ማድረግ አለበት፡፡
6. በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 5 ላይ በተደነገገው መሠረት ተበዳሪው ብድሩን መመለስ ካልቻለ እንዲከፍል የተደረገው ጥረት ቃለ-ጉባዔ ለሥራ አመራር ኮሚቴ ወይም ቦርድ ወይም ሥራ አስኪያጅ በማቅረብ ውሳኔ እንዲሰጥበት መደረግ አለበት፡፡
7. ማንኛውም የቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበር ተበዳሪው የወሰደውን ብድር ለታለመለት ተግባር እያዋለ አለመሆኑን ባደረገው ክትትል ካረጋገጠ ገንዘቡን እንዲመልስ ሊያደርግ ይችላል፡፡
8. ማንኛውም የቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበር የተበዳሪ/ዎችን ጥያቄ መሠረት በማድረግ የብድር የመመለሻ ጊዜ ሊያራዝም ይችላል፡፡
9. በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 8 ላይ የተደነገገው የብድር መመለሻ ጊዜን ማራዘም ተግባራዊ የሚሆነው ከዚህ በታች በተዘረዘሩ ነጥቦች መሰረት ይሆናል፡-

ሀ) ተበዳሪው ብድር እንዲራዘምለት ለኅብረት ሥራ ማህበሩ ጥያቄ አቅርቦ ተቀባይነት ካገኘ፣

ለ) የብድር የማራዘም ውሳኔ ለተበዳሪው ዋስ ቀርቦ ተቀባይነት ካገኘ፣

ሐ) ተበዳሪው ከአቅም በላይ የሆነ ችግር ያጋጠመው መሆኑ በማስረጃ ሲረጋገጥ፣

መ) በተፈጥሮ ወይም ሰው ሰራሽ አደጋዎች ምክንያት ከአቅም በላይ ሆነ ችግር ማጋጠሙ በማስረጃ ሲረጋገጥ፣

10. ብድር የመመለሻ ጊዜ ምን ያህል መራዘም እንዳለበት በኅብረት ሥራ ማህበሩ የብድር አሰራር ስርዓት ውስጥ ተደንግጎ ተግባራዊ መደረግ አለበት።

22) በገንዘብ ቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበራት በወቅቱ ላልተመለሰ ብድር ላይ ስለሚሰጡ ውሳኔዎች

1. የተሰጡ ብድሮች ክትትል ተደርጎበት የመመለሻ ጊዜው ደርሶ እየተመለሰ አለመሆኑ እና ጉዳዩ ከብድር ባለሙያ ወይም የብድር የሥራ ክፍል ወይም ከብድር ኮሚቴ አቅም በላይ መሆኑ ሲረጋገጥ ያልተመለሰበት ምክንያት የሚገልጽ ዝርዝር ሪፖርት ተዘጋጅቶ ለሥራ አመራር ኮሚቴ ወይም ቦርድ ቀርቦ ውሳኔ ሊሰጥበት ይገባል።
2. የብድር ባለሙያ ወይም የብድር ክፍል ወይም ሥራ አሲኪያጅ ወይም የብድር ኮሚቴ ወይም የሥራ አመራር ኮሚቴ ወይም ቦርድ ጊዜው ደርሶ ላልተመለሰ ብድር በቅደም ተከተል በተሰጣቸው ኃላፊነት ተጠያቂ ይሆናሉ፣
3. ያልተመለሰ ብድር ለማስመለስ ከዚህ በታች የተገለጹ ተግባራት ተፈጻሚ መሆን አለባቸው፡-

ሀ) የብድር ባለሙያ ወይም የብድር ኮሚቴ የብድር አመላለሱ የተቋረጠበትን ምክንያት ተበዳሪውን እና ዋሱን በአካል በማግኘት ማነጋገር አለባቸው።

ለ) በውይይቱ ላይ በተደረሰው ስምምነት መሠረት ተበዳሪው ብድሩን ውይይቱ ከተደረገበት ቀን ጀምሮ በ15 ቀናት ውስጥ መመለስ ካልጀመረ የመጀመሪያ የጹሑፍ ማስጠንቀቂያ ለተበዳሪው እና ለዋሱ መሰጠት አለበት።

ሐ) ተበዳሪው አሁንም ግዴታውን አውቆ ብድሩን መመለስ ካልጀመረ ወይም ብድሩን የቋረጠበት በቂ ምክንያት ማቅረብ ካልቻለ ለብድር ዋስትና የተያዘው ንብረት ለብድር ማካካሻነት እንዲውል ይደረጋል።

4. በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 1-3 በተቀመጠው መሰረት ከአንድ ዓመት በላይ የሆነውን በወቅቱ ያልተመለሰ ብድር ከብድር መጠባበቂያ ላይ በመተካትና ከሂሳብ ውስጥ በመሰረዝ ለብቻው ተመዝግቦ እንዲመለስ ክትትል መደረግ አለበት፡፡

23) **የቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበራት የብድር መረጃ አያያዝ እና አስተዳደር፣**

1. የብድር ሰነዶችን በኅብረት ሥራ ማህበሩ በጥንቃቄ መያዛቸውን በየጊዜው ማረጋገጥ ያስፈልጋል፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 1 ላይ የተደነገገው የብድር መረጃ አያያዝን አስመልክቶ በኅብረት ሥራ ማህበሩ የውስጥ የብድር አሰራር ስርዓት ውስጥ በዝርዝር መቀመጥ አለበት፡፡
3. በኅብረት ሥራ ማህበሩ በዋናነት መያዝ የሚገባቸው የብድር ሰነዶች የሚከተሉትን ማካተት አለበት፡-

   ሀ) በተበዳሪው የቀረበ የተሟላ የብድር ማመልከቻ ሰነድ፣

   ለ) የብድር ኮሚቴ ወይም ባለሙያ ውሳኔ የሰጠበት የቃለ-ጉባዔ ሰነድ፣

   ሐ) በኅብረት ሥራ ማህበሩ የተዘጋጁ ብድሩ የተፈቀደበት ቅጹ-ቅፆች፣

   መ) የጸደቀ የብድር ውል፣

   ሠ) የወጭ ማዘዣዎች፣

   ረ) በተበዳሪው የተከፈለና በመከፈል ላይ የሚገኝ ብድር ካለ፣

   ሰ) በዋስትናነት የተያዙ ሕጋዊ ንብረቶች እና ሕጋዊ ማረጋገጫ ሰነዶች፣

   ሸ) ሌሎች ተፈላጊ ሰነዶች፣
4. የቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበሩ የብድር ሰነዶችን የያዘ የብድር ኮሚቴ ወይም ቅጥር ሰራተኛ ከቦታው ሲለቅ ከብድር ጋር የተያያዙ መረጃዎችን አረጋግጦ ለተተኪው ማስረከብ አለበት፡፡

24) **የቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበራት የብድር አተገባበር፣ ክትትልና ቁጥጥር አሰራር ስርዓት፡-**

1. የኅብረት ሥራ ማህበሩ የብድር ኮሚቴ ወይም ባለሙያ የብድር አመላለስ አፈጻጸም በየጊዜው በመከታተል ለሥራ አመራር ኮሚቴ ወይም ቦርድ በማቅረብ ክትትል እንዲደረግበት ማደረግ አለበት፡፡
2. የብድር ኮሚቴ ወይም ባለሙያ እና የሚመለከታቸው አካላት የሚከተሉትን የብድር ክትትል ተግባራት ማከናዎን አለባቸው፤

ሀ) የተበዳሪውን የብድር አጠቃቀም በቅርበት መከታተልና መደገፍ፣

ለ) ተበዳሪው የተበደረውን ብድር ለታለመለት ተግባር እያዋለ ስለመሆኑ መከታተል፣

ሐ) በግንዛቤ ማነስ ምክንያት ብድሩን ላልተፈለገ ተግባር እንዳያውል መደገፍ፣

መ) እየተመለሱ ያልሆኑት ብድሮችን በመለየት የማስተካከያ እርምጃ እንዲወሰድ ማድረግ፣

ክፍል አራት

አነስተኛ የኢንሹራንስ አገልግሎት አሰጣጥ ስርዓት

25) የቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበራት አነስተኛ የኢንሹራንስ አገልግሎት አሰጣጥ ስርዓት

1. አነስተኛ የኢንሹራንስ አገልግሎት ዓላማ በአባላት ላይ ሊደርስ የሚችለውን ጉዳት እና በገንዘብ ቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበሩ ላይ ሊደርስ የሚችለውን ኪሳራ በመቀነስ ውጤታማ እንዲሆኑ ለማድረግ መሆን አለበት፡፡
2. አነስተኛ የኢንሹራንስ አገልግሎት ተጠቃሚው በገባው የኢንሹራንስ ዓይነትና መጠን ልክ የሚደርሰውን ጉዳት ወይም ኪሳራን ከመሸፈን ባሻገር የሚከፈለው ካሳ ሌላ ትርፍ ማስገኘነት የለበትም፣
3. አነስተኛ የኢንሹራንስ አገልግሎት የሚሰጡ የቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበራት አገልግሎቱን ተግባራዊ ከማድረጋቸው በፊት አስፈላጊውን ቅድመ-ዝግጅት ማድረግ አለባቸው፤
4. በገንዘብ ቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበራት የሚሰጠው አነስተኛ የኢንሹራንስ አገልግሎት አሰጣጥ ከዚህ በታች በተመለከተው መሰረት ተፈፃሚ መሆን አለበት፤
   ሀ) አነስተኛ የኢንሹራንስ አገልግሎት ለተገልጋዮች ክብር በመስጠትና ወጪ ቆጣቢ በሆነ መንገድ መስጠት አለበት፣
   ለ) የሚቀርበው አነስተኛ የኢንሹራንስ አገልግሎት ለተገልጋዮች ተስማሚ፣ ዋጋው ተመጣጣኝና ቀጣይነት ባለው መልኩ ማቅረብ አለበት፣
   ሐ) የአነስተኛ የኢንሹራንስ አገልግሎት ውል አፈፃፀም በቅን ልቦና፣ በፈቃደኝነትና በትክክለኛ መረጃ ላይ መመስረት አለበት፣

መ) የቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበራት ለአነስተኛ የኢንሹራንስ አገልግሎት ተጠቃሚ ለደረሰው ጉዳት የሚከፍሉት ካሳ በገንዘብ ይሆናል፣

5. የቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበራት አነስተኛ የኢንሹራንስ አገልግሎት የሚሰጡት ከዚህ በታች በተቀመው አሰራር መሰረት ሊሆን ይችላል፤

ሀ) መሠረታዊ የቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበራት አነስተኛ የኢንሹራንስ አገልግሎት ሰጪ ሆኖ ቀጥታ ለአባላት ሊሰጡ ይችላሉ፣

ለ) የቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበራት ዩኒየን አነስተኛ የኢንሹራንስ አገልግሎት ሰጪ ሆኖ መሠረታዊ የቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበራት በውክልና ለአባላት ሊሰጡ ይችላሉ፣

ሐ) የቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበራት ፌዴሬሽን አነስተኛ የኢንሹራንስ አገልግሎት ሰጪ ሆኖ የቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበራት ዩኒየን ወይም መሠረታዊ የቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበራት በውክልና ለአባላት ሊሰጡ ይችላሉ፣

መ) የቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበራት ፌዴሬሽን ወይም ዩኒየኖች ወይም መሠረታዊ የቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበራት ከሌሎች የኢንሹራንስ ሰጪ ተቋማት ጋር የውል ስምምነት በመግባት በውክልና አነስተኛ የኢንሹራንስ አገልግሎት ለተጠቃዎች ሊሰጡ ይችላሉ፣

6. በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 6 (ለ እና ሐ) ላይ የተጠቀሰው ግለሰብ አባላት ከገንዘብ ቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበራት ዩኒየን ወይም ፌዴሬሽን በቀጥታ በመገናኘት አገልግሎት ማግኘት የሚችሉት መሠረታዊ የቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበራቸው አገልግሎት መስጠት የማይችል መሆኑ ሲረጋገጥ ብቻ ይሆናል።

26) የቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበራት በአነስተኛ የኢንሹራንስ አገልግሎት አሰጣጥ የኢንሹራንስ ሰጪ፣ ተወካይ እና ተጠቃሚ ተግባርና ኃላፊነት እንዲሁም መብትና ግዴታ፣

1. አነስተኛ የኢንሹራንስ አገልግሎት ሰጪ ተግባርና ኃላፊነት ከዚህ በታች የተዘረዘሩት ሊሆን ይችላል፤

ሀ) የሚሰጠውን አነስተኛ የኢንሹራንስ አገልግሎት ዓይነት በጥናት መለየት፣

ለ) አገልግሎቱን ለመስጠት የሚያስችል አሰራሮችን መዘርጋት፣

ሐ) አገልግሎቱን ለመስጠት የህብረተሰቡን ሞራላዊ እሴቶችን በጠበቀ መልኩ የውል ሰነድ ማዘጋጀት፣

መ) አገልግሎቱን ለመስጠት ተጠቃሚዎችን ወይም በውክልና አገልግሎቱን የሚሰጡትን አካላት መለየት፣

ሠ) በሚሰጧቸው አነስተኛ የኢንሹራንስ አገልግሎቶች ላይ ለተጠቃሚዎች ግንዛቤ መስጠት፣

2. የአነስተኛ የኢንሹራንስ አገልግሎት ሰጪው ከዚህ በታች የተዘረዘሩት መብቶች ሊኖሩት ይችላል

ሀ) የአረቦን ምጣኔ መወሰንና መሰብሰብ፣

ለ) ከወኪሉ ወይም ከተጠቃሚው ሪፖርት ማግኘት፣

ሐ) የደንበኛውን ሙሉ መረጃ ከወኪሉ ወይም ከተጠቃሚው የማግኘት፣

መ) የካሳ ክፍያ ከመፈጸሙ በፊት ስለ ጉዳቱ መረጃ የመጠየቅና የማጣራት፣ መብት ይኖረዋል፡፡

3. አነስተኛ የኢንሹራንስ አገልግሎት ሰጪ ከዚህ በታች የተዘረዘሩት ግዴታዎች አለበት ፡

ሀ) የካሳ ጥያቄ በቀረበለት ጊዜ ለወራሹ በውሉ መሰረት ክፍያ መፈፀም፣

ለ) የወኪሉን ወይም የተጠቃሚውን መብት በውሉ መሠረት ማክበርና መፈፀም፣

ሐ) በሚሰጠው የአነስተኛ የኢንሹራንስ አገልግሎት ላይ ለሚመለከታቸው አካላት ግንዛቤ መፍጠር፣

መ) በሚሰጡ አገልግሎቶች ላይ ከወኪል ወይም ከተጠቃሚው ጋር የውል ስምምነተ መፈፀም፣

ሠ) በውል ስምምነቱ መሰረት ለወኪል ኮሚሽን መክፈል፣

ረ) ቅሬታ የሚስተናገድበትና የሚፈታበት ስርአት መዘርጋትና መተግበር፣

ሰ) በሚሰጠው የኢንሹራንስ አገልግሎት ላይ ዝርዝር መግለጫ መስጠት፣

ሸ) የተሻሻሉና የተቀረፁ አነስተኛ የኢንሹራንስ አገልግሎቶችን ለተጠቃሚዎች ግልፅ ማድረግ፣

ቀ) ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመቀናጀት የአረቦን ምጣኔ እየገመገሙ ክለሳ ማድረግ፣

በ) ለሚመለከተው አካል በወቅቱ ሪፖርት የማቅረብ፣

ተ) የአገልግሎት ተጠቃሚውን ሚስጥር የመጠበቅ፣

4. አነስተኛ የኢንሹራንስ አገልግሎት ሰጪ ወኪል ተግባርና ኃላፊነት ከዚህ በታች የተዘረዘሩት ሊሆን ይችላል ፡

ሀ) የአነስተኛ የኢንሹራንስ አገልግሎት ተጠቃሚዎችን መለየት፣

ለ) የአነስተኛ የኢንሹራንስ አገልግሎት ተጠቃሚዎች አገልግሎቱን ለማግኘት የሚያስችላቸውን መስፈርት ማሟላታቸውን ማረጋገጥ፣

ሐ) በሚሰጡ አነስተኛ የኢንሹራንስ አገልግሎቶች ላይ ለተጠቃሚዎች ግንዛቤ መፍጠር፣

መ) አነስተኛ የኢንሹራንስ አገልግሎቱን ከተጠቃሚዎች ጋር ውል በመግባት መሸጥ፣

ሠ) የአነስተኛ የኢንሹራንስ አገልግሎቱን ከተጠቃሚዎች አረቦን መሰብሰብና ለአገልግሎት ሰጪው ማስተላለፍ፣

ረ) በሚሰጠው የአነስተኛ የኢንሹራንስ አገልግሎት ላይ ለተጠቃሚዎች ድጋፍና ክትትል ማድረግ፣

5. አነስተኛ የኢንሹራንስ አገልግሎት ሰጪ ወኪል ከዚህ በታች የተዘረዘሩት መብቶች ሊኖሩት ይችላል፡፡

ሀ) በስምምነቱ መሰረት ኮሚሽን የማግኘት ፣.

ለ) የኢንሹራንስ አገልግሎት ካሳን ለተጠቃሚዎች የመጠየቅ፣

ሐ) ላስለላለፈው አረቦን ህጋዊ ደረሰኝ ከአገልግሎት ሰጪው የማግኘት፣

መ) የኢንሹራንስ አገልግሎት የአቅም ግንባታ ድጋፍ የማግኘት፤

ሠ) ከተጠቃሚዎች አስፈላጊውን መረጃ የማግኘትና የማጣራት፣

6. አነስተኛ የኢንሹራንስ አገልግሎት ሰጪ ወኪል ከዚህ በታች የተዘረዘሩት ግዴታዎች አለበት፡

ሀ) የተጠቃሚዎችን መረጃ የመሰብሰብና የመተንተንና ፣

ለ) አረቦን ከተጠቃሚዎች መሰብሰብና በውሉ መሠረት ለአገልግሎት ሰጪው ማስተላለፍ፣

ሐ) ተጠቃሚው ለደረሰበት አደጋ በማመልከቻ ሲያቀርብ አግባብነቱን በማጣራት ካሳ እንዲከፈለው ለአገልገሎት ሰጪው ጥያቄ የማቅረብ፣

መ) የካሳ ክፍያውን ከኢንሹራንስ አገልግሎት ሰጪው በመቀበል በውሉ መሠረት ለተጠቃሚው መክፈል፣

ሠ) የአነስተኛ የኢንሹራንስ አገልግሎት ሰጪው በውሉ መሠረት ለወኪል የካሳ ክፍያውን በወቅቱ ካልፈፀመ ወኪሉ ለተጠቃሚው ከፍሎ ከአገልግሎት ሰጪው በውሉ መሠረት የመቀበል፣

ረ) የአገልግሎት ተጠቃሚውን ሚስጥር የመጠበቅ፣

7. አነስተኛ የኢንሹራንስ አገልግሎት ተጠቃሚ ከዚህ በታች የተዘረዘሩት መብቶች ሊኖሩት ይችላል፡

ሀ) የሚሰጠውን የኢንሹራንስ አገልግሎት በህጉ መሰረት የመጠቀም፣

ለ) አደጋ ሲያጋጥም በውል ስምምነታቸው መሰረት ካሳ የማግኘት ፣

ሐ) ወኪልና አገልግሎት ሰጪው ሚስጥሩን እንዲጠብቁለት የማድረግ፣

መ) ስለአገልግሎቱ ግልጽ ማብራሪያ የመጠየቅ፣

ሠ) ከወኪሉ ወይም አገልገሎት ሰጪው ምክር ሃሳብ የማግኘት፣

8. አነስተኛ የኢንሹራንስ አገልግሎት ተጠቃሚ ከዚህ በታች የተዘረዘሩት ግዴታዎች አለበት፡

ሀ) የሚሰጠው አገልግሎት ቁጠባን መሰረት ያደረገ አነስተኛ የኢንሹራንስ አገልግሎት ከሆነ ተጠቃሚው መደበኛ ቁጠባውን በተከታታይ የመቆጠብ፣

ለ) በውል ስምምነቱ መሰረት አረቦን የመክፈል፣

ሐ) ተጠቃሚው የውል ዘመኑ ከመጠናቀቁ በፊት ጉዳት ቢደርስበት በራሱ ወይም በህጋዊ ወራሹ አማካኝነት ለካሳ ማመልከቻና መረጃ የማቅረብ፣

መ) አነስተኛ ኢንሹራንስ የተገባለትን ንብረት በጥንቃቄ የመጠቀምና የመጠበቅ፣

ሠ) ተጠቃሚው በቅን ልቦናና ታማኝነት አገልግሎቱንና ንብረቱን የመጠቀም፣

27) በገንዘብ ቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማኅበራት የሚሰጥ አነስተኛ የኢንሹራንስ አገልግሎት አሰጣጥና አተገባበር

1. ማንኛውም የቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበር የአባላትን ፍላጎትና ምቹ ሁኔታዎችን በማጥናትና በመለየት አነስተኛ ኢንሹራንስ አገልግሎትን መስጠት ይችላሉ፤
2. አዳዲስ የአነስተኛ ኢንሹራንስ አገልግሎት ተግባራዊ ከመደረጉ በፊት አግባብ ላለው ባለስልጣን ቀርቦ መመዝገብ አለበት፣
3. አነስተኛ የኢንሹራንስ አገልግሎቱ ከመሰጠቱ በፊት አሰራር ስርዓት መዘርጋት አለበት፣

4. ማንኛውም የቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበር ከሌሎች የኢንሹራንስ ሰጪ ድርጅቶች ጋር በስምምነት የሚሰጠው የአነስተኛ የኢንሹራንስ አገልግሎት ተግባራዊ የሚያደርገው አግባብ ላለው ባለስልጣን ሲፈቀድ ብቻ ይሆናል፣

28) **የአነስተኛ የኢንሹራንስ አገልግሎት የአረቦን አወሳሰን፣ አሰባሰብና አስተዳደር**

1. ማንኛውም የቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበር ለሚሰጠው የአነስተኛ የኢንሹራንስ አገልግሎት አረቦን መሰብሰብ አለበት፣
2. በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 1 ላይ የተጠቀሰው የአረቦን አወሳሰን የሚደርሰውን የአደጋ መጠን፣ የአደጋ ድግግሞሽ፣ የሥራ ማስኪጃ ወጪዎች እና መጠነኛ ትርፍን ታሳቢ በማድረግ ሊወሰን ይችላል፡፡
3. የቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበራት የአረቦን ምጣኔ መጠን እንደ አነስተኛ የኢንሹራንስ አገልግሎቱ ዓይነት ሊለያይ ይችላል፡፡
4. የአነስተኛ የኢንሹራንስ አገልግሎት አረቦን ክፍያ መሰብሰብ የሚጀምረው ውል ከተገባበት ቀን ጀምሮ ይሆናል፣
5. የአነስተኛ የኢንሹራንስ አገልግሎት ሰጪው አረቦን የሚሰበሰብው በጥሬ ገንዘብ ወይም በወለድ ወይም ከሚሰጠው ብድር በመቀነስ ሊሆን ይችላል፡፡
6. በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 5 ላይ የተቀመጠው የአረቦን አሰባሰብ እንደተጠበቀ ሆኖ የኢንሹራንስ አገልግሎት ሰጪው ሊያሰራ የሚችለውን የአረቦን አሰባሰብ አሰራር ሊወስን ይችላል፡፡
7. አነስተኛ የኢንሹራንስ አገልግሎት ሰጪ አካላት በአረቦን ምጣኔ ላይ ጥናት በማድረግ ምጣኔውን መከለስና ማሻሻል ይችላሉ፣
8. የአነስተኛ የኢንሹራንስ አገልግሎት ሰጪ አካል በውል ስምምነት መሠረት ለወኪሉ ኮሚሽን መክፈል ይችላል፡፡
9. በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 8 የተደነገገው የኮሚሽን ክፍያ ታሳቢ የሚያደርገው በሚሰጠው አገልግሎት ዓይነትና አገልግሎቱን ለመስጠት በሚጠይቀው ወጪ መሰረት ማድረግ አለበት፡
10. የአነስተኛ የኢንሹራንስ አገልግሎት የተጠቃሚነት ጊዜ በአገልግሎት ሰጪውና ተጠቃሚው በሚደረግ የውል ስምምነት መሠረት ተፈፃሚ መሆን አለበት፣
11. የአነስተኛ የኢንሹራንስ አገልግሎት የሚሰጡ አካላት አገልግሎቱን ለመስጠት የሚያስችል የውል ስምምነት ሰነድ አዘጋጅተው አገልግሎቱን መስጠት አለባቸው፤

29) **የአነስተኛ መድን ዋስትና የካሳ ክፍያ አጠያየቅና አከፋፈል ስርዓት**

1. የአነስተኛ የኢንሹራንስ አገልግሎት የካሳ ክፍያ አጠያየቅ ሂደት ተጠቃሚውን፣ ወኪሉን እና አገልግሎት ሰጪውን በቅደም ተከተል የሚያሳትፍ መሆን አለበት፣
2. የአነስተኛ የኢንሹራንስ አገልግሎት የካሳ ክፍያ አከፋፈል ሂደት አገልግሎት ሰጪው፣ወኪሉንና ተጠቃሚውን በቅደም ተከተል የሚያሳትፍ መሆን አለበት፣
3. ለተጠቃሚዎች በቀጥታ ለሚከፈለው የአነስተኛ የኢንሹራንስ አገልግሎት ካሳ ክፍያ ተግባራዊ የሚሆነው ከዚህ በታች በተጠቀሰው መሠረት ይሆናል፣
   ሀ) ህጋዊ ወራሽ ወይም ተጠቃሚው ማመልከቻውን ከማስረጃ ጋር በማያያዝ ለአገልግሎት ሰጪው ሪፖርት ማቅረብ፣
   ለ) አገልግሎት ሰጪው የቀረበለትን ማስረጃዎች በማጣራት፣
   ሐ) በሂሳብ ክፍል ያለውን መረጃ በማሰባሰብ ያለውን ሃብትና ዕዳ በመለየት ያበለበትን ዕዳ ማጣራት
   መ) በውሉ መሠረት የካሳ ክፍያ መፈፀም፣
4. በአነስተኛ የኢንሹራንስ አገልግሎት ሰጪና ወኪል በሚሰጥ አገልግሎት ተግባራዊ ሊሆኑ የሚገባቸው የካሳ አጠያየቅ ሂደቶች ከዚህ በታች በተጠቀሰው መሠረት ይሆናል
   ሀ) ህጋዊ ወራሽ ወይም ተጠቃሚው ለወኪል ወይም አገልግሎት ሰጪው በማመልከቻ ከሌሎች ደጋፊ ሰነዶች ጋር በማያያዝ ማቅረብ አለበት፤
   ለ) መረጃ የቀረበለት አካል የመረጃውን አግባብነት ማረጋገጥ አለበት፤
   ሐ) በሂሳብ ክፍል ውስጥ ያለውን መረጃ በማሰባሰብ ሃብትና ዕዳውን በመለየት ያበለበትን ዕዳ ማጣራት
   መ) በውሉ መሠረት የካሳ ክፍያ መፈፀም ፣
5. የአነስተኛ ኢንሹራንስ አገልግሎት የካሳ ክፍያ ጥያቄ ከዚህ በታች በተዘረዘሩ ምክንያቶች ውድቅ ሊደረግ ይችላል፤
   ሀ/ የቀረበው የካሳ ክፍያ ጥያቄ በአነስተኛ የኢንሹራንስ አገልግሎት የተገባለት አደጋ ካልሆነ፣
   ለ/ የካሳ ክፍያ ጥያቄው የውል ዘመኑ ከተጠናቀቀ በኂላ የቀረበ ከሆነ፣

30) **በአነስተኛ የኢንሹራንስ አገልግሎት የሚሸፈኑና የማይሸፈኑ ጉዳዩችና የመረጃ አያያዝ**

1. በአነስተኛ የኢንሹራንስ አገልግሎት የሚሸፈኑ ጉዳዮች በገንዘብ ለሚተመኑና ኪሳራ ለሚያስከትሉ አደጋዎች ብቻ መሆን አለበት፣
2. የሚከተሉት አደጋዎች በአነስተኛ የኢንሹራንስ አገልግሎት ሊሸፈኑ አይችሉም፤
   ሀ/ በተፈጥሮ አደጋ ምክንያት ማለትም ድርቅ፣ ጎርፍ፣ የመሬት መንቀጥቀጥ፣ ሰደድ እሳት፣ ወረርሽኝ የሚከሰት አደጋ፣
   ለ/ ሰው ሰራሽ አደጋዎች ማለትም ጦርነት፣የብሔር ወይም የጎሳ ግጭት፣
   ሐ/ ማጭበርበር፣ ማታለል
   መ/ ሆን ብሎ ራስን ያጠፋ
   ሠ) ተጠቃሚው ወንጀል ሰርቶ ለማምለጥ ሲሞክር ጉዳት ከደረሰበት
3. ማንኛውም የቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበር የአነስተኛ የኢንሹራንስ አገልግሎት መረጃዎች አሟልቶ በመያዝ ተግባራዊ ማድረግ አለበት፣
4. አነስተኛ የኢንሹራንስ አገልግሎት የሚሰጡ የቁጠባና ብድር የኅብረት ሥራ ማህበራት ከአነስተኛ የኢንሹራንስ የአገልግሎት ጋር በተያያዘ የተለዩ የፋይናንስ መግለጫዎችን ማዘጋጀት ይኖርባቸዋል፤
5. ማንኛውም የአነስተኛ የኢንሹራንስ አገልግሎት የሚሰጥ የቁጠባና ብድር የኅብረት ሥራ ማህበር የሰበሰበው አረቦን ከሚሸፍነው የፋይናንስ አቅም በላይ ሊያጋጥም ለሚችል አደጋ ለመሸፈን የሚያስችል መጠባበቂያ ገንዘብ በጠቅላላ ጉባኤ በማስወሰን መያዝ ይችላሉ፣

ክፍል አምስት

የወለድ አልባ የፋይናንስ አገልግሎት አስተዳደር

31) የወለድ አልባ የፋይናንስ አገልግሎትን ስለመስጠት

1. ማንኛውም የቁጠባና ብድር ኅብረት ስራ ማህበር የሸሪዓ ህግን መሠረት ያደረገ የወለድ አልባ የፋይናንስ አገልግሎት በመስኮት ለአባላት መስጠት ይችላል፤
2. የቁጠባና ብድር ኅብረት ስራ ማህበር አዳዲስ የወለድ አልባ የቁጠባ፣ የብድር እና የተካፉል የፋይናንስ አገልግሎት ዓይነቶችን በማጥናትና በመቅረፅ አገልግሎቱን ማስፋፋት ይችላል፤

3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 የተጠቀሱት አዳዲስ የተቀረፁ የፋይናንስ አገልግሎቶች ከመተግበራቸው በፊት አግባብ ባለው ባለስልጣን መፅደቅና መመዝገብ አለባቸው፤
4. በመስኮት ወለድ አልባ የፋይናንስ አገልግሎት የሚሰጥ ማንኛውም የቁጠባና ብድር ኅብረት ስራ ማህበር ፍትሃዊ የሆነ አገልግሎትን ለአባላት ማቅረብ አለበት፤
5. ማንኛውም የቁጠባና ብድር ኅብረት ስራ ማህበር የወለድ አልባ የፋይናንስ አገልግሎትን መስጠት ከመጀመሩ አስቀድሞ የሚከተሉትን ቅድመ-ሁኔታዎች ማሟላት አለበት፤
   ሀ) የአባላትን እና ወደፊት አባል ሊሆኑ የሚችሉትን ፍላጎት መለየት፤
   ለ) የኅብረት ስራ ማህበሩን ነባራዊ ሁኔታ መተንተን፤
   ሐ) ስለአገልግሎቱ ምንነት ለአባላት እና ለኅብረተሰቡ ግንዛቤ ማስጨበጥ፤
   መ) የወለድ አልባ የፋይናንስ አገልግሎቶችን ያካተተ መተዳደሪያ ደንብ ማዘጋጀት ወይም ማሻሻል፤
   ሠ) የወለድ አልባ የባንክ ሂሳብ ቁጥር መክፈት፤
   ረ) ለወለድ አልባ የፋይናንስ አገልግሎት የሚውሉ ሂሳብ ነክ የሆኑ እና ያልሆኑ ሰነዶችን፣ የውል ስምምነቶችን፣ ቅፆችን እና መዛግብቶችን ማዘጋጀት ወይም ማሻሻል፤
   ሰ) ወለድ አልባ የፋይናንስ አገልግሎትን መጠቀም የሚፈልጉ አባላትን በተዘጋጀው ቅጽ ላይ በማስፈረም ስምምነታቸውን እንዲገልፁ ማስደረግ፤

32) **የወለድ አልባ የፋይናንስ አገልግሎት መርሆዎች**

ማንኛውም የወለድ አልባ የፋይናንስ አገልግሎትን የሚሰጥ የቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበር የሚከተሉትን መርሆዎች መከተል አለበት፤

ሀ) ጥሬ ገንዘብ እውነተኛ ዋጋ የሌለውና ገንዘብ የማይሸጥ፣ የማይለወጥና ለቆየበት ጊዜ ዋጋው ሊጨምር የማይችል የሃብት ክፋይ መሆኑ፤

ለ) በውል መሠረት ትርፍና ኪሳራን መጋራት

ሐ) ያለቀለት ምርት ወይም ዕቃ ለአገልግሎት ማቅረብ፤

መ) በተበዳሪው ላይ ጫና የማያሳድር ስምምነት የሚከተል መሆኑ፤

ሠ) በሸሪዓው ለተከለከሉ የሥራ መስኮች እና ለማህበረሰቡ ጎጂ ለሆኑ ተግባሮች የፋይናንስ አገልግሎት መስጠት የማይፈቅድ መሆኑ፤

33) **የሸሪዓ አሰራር ቅድመ ሁኔታዎች**

1. ማንኛውም የቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበር በወለድ ለሚሰጥ እና በወለድ አልባ ለሚሰጠው የፋይናንስ አገልግሎት የሚውል ፈንድ ለየብቻ መለየት አለበት፤
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 መሠረት ፈንድ የመለየት ተግባር ከዚህ በታች በተቀመጠው መሰረት ተፈፃሚ መሆን አለበት፤
   ሀ) ነባር የቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበር በወለድ ሲሰጥ ከነበረው ፈንድ ውስጥ የወለድ አልባ ተጠቃሚዎችን የተጣራ ቁጠባና ዕጣ በመለየት ለብቻ ማስቀመጥ፤
   ለ) ከወለድ ጋር ከማይገናኙ ምንጮች የተገኘን ገንዘብ ወይም ፈንድ ለወለድ አልባ የፋይናንስ አገልግሎት እንዲውል በማድረግ፤
   ሐ) የወለድ አልባ የፋይናንስ አገልግሎት የፋይናንስ ምንጭ ከወለድ ጋር የማይገናኝ መሆኑ በሸሪዓ አማካሪ ቦርድ ሲረጋገጥ፣
3. ማንኛውም የቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበር ወለድ አልባ የፋይናንስ አገልግሎት ለመስጠት ከ3-5 አባላት ያሉት የሸሪዓ አማካሪ ቦርድ ሊኖረው ይገባል።
4. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 3 ላይ የተቀመጠው የሸሪዓ አማካሪ ቦርድ አመራረጥ ከዚህ በታች በተቀመጡ መስፈርቶች መሰረት ይሆናል።
   ሀ) ስለሸሪዓ አሰራር በቂ ዕውቀት ያለው፤
   ለ) በአካባቢው ህብረተሰብ ተቀባይነት ያለው፤
5. የሸሪዓ አማካሪ ቦርድ ከዚህ በታች የተገለጹት ተግባርና ሃላፊነት ይኖረዋል፤
   ሀ) ከማንም ተፅዕኖ ነፃና ገለልተኛ በመሆን ሸሪዓዊ ውሳኔዎች መስጠት፤
   ለ) በአገልግሎቱ አተገባበር ላይ የማማከር አገልግሎት መስጠት፤
   ሐ) በአገልግሎቱ አተገባበር ሂደት ላይ መደገፍ፣ መከታተል እና መቆጣጠር፤
6. ማንኛውም የቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበር የወለድ አልባ የፋይናንስ አገልግሎትን ለመስጠት ለሸሪዓ ቅድመ-ሁኔታዎች እና መርሆዎች ተገዥና ቁርጠኛ የሆኑ የአመራር አካላት ሊኖረው ይገባል።
7. ማንኛውም የቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበር የአባላትን ገንዘብ የሸሪዓ መር የፋይናንስ አገልግሎት በሚፈቅደው አሰራር መሰረት ማስተዳደርና ደህንነቱን ማስጠበቅ አለበት፤

34) የቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበር የወለድ አልባ የቁጠባ አሰባሰብና አጠቃቀም ስርዓት

1. የቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበር መደበኛ ቁጠባን የሚሰበስበው በዋዲዓ የድ ደማን የቁጠባ አገልግሎት መሆን አለበት፤

2. በዚህ *መመሪያ* በአንቀፅ 4 ከንዑስ አንቀፅ (2-9) የተቀመጡ የቁጠባ አሰባሰብ ሂደቶች እንደተጠበቁ ሆኖ የወለድ አልባ የፋይናንስ አገልግሎት በተጨማሪም የሚከተሉትን ማካተት አለበት፤

   ሀ. የተሰበሰበውን ቁጠባ በተከፈተው ወለድ አልባ የባንክ አካውንት የማስቀመጥ፤

   ለ. በዋዲዓ የድ ደማን መደበኛ የወለድ አልባ ቁጠባ የተሰበሰበ ገንዘብን በወለድ አልባ የብድር አገልግሎቶች ላይ ብቻ የማዋል፤

3. የቁጠባና ብድር ኅብረት ስራ ማህበሩ በዋዲዓ የድ ደማን ለሰበሰበው መደበኛ ቁጠባ አባላትን ለማበረታታት ሽልማት ሊሰጥ ይችላል።

4. የወለድ አልባ የፋይናንስ አገልግሎትን የሚሰጥ ማንኛውም የቁጠባና ብድር ኅብረት *ሥራ* ማህበር ከአባላት የፍላጎት የወለድ አልባ ቁጠባን መሰብሰብ ችላል፤

5. በዚህ *መመሪያ* አንቀፅ 5 ከንዑስ አንቀፅ 1-4 የተቀመጠው ለወለድ አልባ የፋይናንስ አገልግሎት ላይ የሚተገበር ሆኖ በተጨማሪም የሚከተሉትን ሊያካትት ይችላል፤

   ሀ) የሰበሰበውን የፍላጎት የወለድ አልባ ቁጠባ ለወለድ አልባ የብድር አገልግሎቶች በውል ስምምነቱ *መሠረት* የመጠቀም፤

   ለ) የፍላጎት የወለድ አልባ ቁጠባን ስራ ላይ አውሎ ያገኘውን ትርፍ አባላትን ለማበረታታት ሽልማት ወይም ትርፍ የማካፈል፤

   ሐ) የወለድ አልባ የፍላጎት ቁጠባ ለብድር ዋስትና መያዝ ይችላል፤

6. ማንኛውም የወለድ አልባ የፋይናንስ አገልግሎት የሚሰጥ የቁጠባና ብድር ኅብረት *ሥራ* ማህበር በዚህ *መመሪያ* አንቀፅ 6 ንዑስ-አንቀፅ 1-3 መሰረት የዓይነት ቁጠባ ሊሰበስብ ይችላል።

35) የቁጠባና ብድር ኅብረት *ሥራ* ማህበር ወለድ አልባ የብድር አስተዳደርና አጠቃቀም ስርዓት

1. ማንኛውም የቁጠባና ብድር ኅብረት *ሥራ* ማህበር ለአባላት የወለድ አልባ የብድር አገልግሎቶችን መስጠት ይችላል፤

2. ወለድ አልባ የብድር አገልግሎትን የሚሰጥ ማንኛውም የቁጠባና ብድር ኅብረት *ሥራ* ማህበር እንዳስፈላጊነቱ የብድር ኮሚቴ ሊያቋቁም ወይም የብድር ባለሙያ ሊመድብ ይችላል፣

3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) መሰረት የተቋቋመው የብድር ኮሚቴ ወይም የተመደበ ባለሙያ ተግባርና ሃላፊነቶች በኅብረት ሥራ ማህበሩ መተዳደሪያ ደንብ እና በብድር አስተዳደር አሰራስርዓት የሚወሰን ሆኖ በተለይ የሚከተሉትን ያካትታል፤

ሀ) የወለድ አልባ ብድር ጥያቄ ከተጠቃሚ አባላት መቀበል፤

ለ) የወለድ አልባ የብድር ጥያቄ የአገልግሎቱን ዓይነት መሰረት በማድረግ መገምገምና መወሰን ወይም ለውሳኔ ማቅረብ፤

ሐ) ለወለድ አልባ ብድር አገልግሎት የሚውል በቂ ገንዘብ መኖሩን ማረጋገጥ፤

መ) የወለድ አልባ ብድር አመላለስን መከታተል፤

ሠ) በወለድ አልባ የተሰጠው ብድር ሸሪዓ መር በሆኑ ተግባራት ላይ መዋሉን መከታተል፤

4. በገንዘብ ቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበር በወለድ አልባ የብድር አገልግሎት ለሚከናወኑ ግዥና ሽያጭ ተግባራት የግዥና ሽያጭ ኮሚቴ ማቋቋም ወይም ባለሙያ መመደብ አለበት፡፡

5. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 4 መሰረት የተቋቋመው የግዥና ሽያጭ ኮሚቴ ወይም ባለሙያ ተግባርና ኃላፊነት በኅብረት ሥራ ማህበሩ መተዳደሪያ ደንብ እና በግዥና ሽያጭ አሰራር ስርዓት የሚወሰን ሆኖ በተለይ የሚከተሉትን ያካትታል፤

ሀ) ስለሚገዛው ምርት ወይም አገልግሎት ዓይነት፣ መጠን፣ የገበያ ዋጋ እና በአካባቢው ስለመገኘቱ የገበያ ጥናት ያካሂዳል፤

ለ) ከተካሄደው ጥናት አንጻር የተጠየቀው ምርት ወይም አገልግሎት ላይ ማሻሻያ ካስፈለገው የብድር ጥያቄው እንዲሻሻል ሃሳብ ያቀርባል፤

ሐ) የግዥ ጥያቄው ሲፈቀድለት የሸሪዓ የግብይት ስርዓትን ጠብቆ ግዥ ይፈፅማል፤

ሠ) የተገዛውን ምርት ወይም አገልግሎት ለኅብረት ሥራ ማህበሩ ያስረክባል፤

6. በዚህ መመሪያ አንቀፅ 15 ንዑስ-አንቀፅ 7 (ሀ-ሐ) የተደነገጉ መስፈርቶች እንደተጠበቁ ሁነው የወለድ አልባ የብድር አገልግሎት ተጠቃሚ አባላት በተጨማሪነት የሚከተሉትን መስፈርቶች ማሟላት አለባቸው፤

ሀ) የወለድ አልባ ፋይናንስ አገልግሎት ተጠቃሚ መሆን፤

ለ) በኅብረት ሥራ ማህበሩ እና በአባሉ መካከል ሸሪዓውን የጠበቀ የብድር ውል ስምምነት መፈፀም፤

36) **የሙራባሃ ብድር ስርዓት**

1. ማንኛውም የቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበር የሙራባሃ ብድር አገልግሎት ሲያቀርብ ከዚህ በታች የተዘረዘሩ አሰራሮችን መከተል አለበት፤
   ሀ) ተበዳሪው የግዥ ፍላጎቱን በፅሁፍ ማመልከቻ የማቅረብ፤
   ለ) የተገዛውን ዕቃ ለመረከብ ከገንዘብ ቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበሩ ጋር ውል የመግባት፤
   ሐ) ግዥ የሚፈፀመው በኅብረት ሥራ ማህበሩ ወይም በውክልና ሊሆን ይችላል፤
   መ) የተገዛው ንብረት በኅብረት ሥራ ማህበሩ ገቢ መደረግ አለበት፤
   ሠ) ወጪ ቆጣቢ የግዥ ሂደትን መከተል አለበት፤
   ረ) የተገዛው ንብረት ወደ ተበዳሪው ከመተላለፉ በፊት በተገዛበት ዋጋ ላይ ወጪና የትርፍ ህዳግ በመጨመር የውል ስምምነት መደረግ አለበት፤
   ሰ) ንብረቱን በሰነድ ወጪ ማድረግና አባሉን በማስፈረም ማስረከብ፤
2. የሙራባሃ ብድር የትርፍ ህዳግ የሚወሰነው ከዚህ በታች በተቀመጠው አሰራር መሆን አለበት፤
   ሀ) የትርፍ ህዳጉ የሚሰላው በመቶኛ ስሌት መሆን አለበት፣
   ለ) የትርፍ ህዳግን በመቶኛ ስሌት የአስተዳደራዊ ወጪን፣ ትርፍን እና የማይመለስ ብድር መጠባበቂያን ማካተት አለበት፣
   ሐ) ተመሳሳይ አስተዳደራዊ ወጪ ለሚጠይቁ ተመሳሳይ ግዥዎች ወጥ የሆነ የትርፍ ህዳግን መጠቀም ይቻላል፤
   መ) በልዩ ሁኔታ የተፈፀመ ግዥ ከሆነ የትርፍ ህዳግ የሚቀመጠው ወጪ እና ትርፍን በማስላት ይሆናል፤
3. የሙራባሃ የብድር አመላለስ ከዚህ በታች በተቀመጠው አሰራር መሠረት ተግባራዊ መሆን አለበት፤
   ሀ) ተበዳሪው ብድሩን በጥሬ ገንዘብ መመለስ አለበት፤
   ለ) ተበዳሪው የንብረቱን ዋጋ እና የትርፍ ጭማሪውን በውሉ መሰረት መመለስ አለበት፤
   ሐ) የመመለሻ ጊዜውን ያሳለፈ ተበዳሪ የንብረቱን ዋጋና የትርፍ ጭማሪ ሳይቀየር ቅጣት እንዲከፍል ሊደረግ ይችላል፤
4. በዚህ መመሪያ አንቀፅ 18 ላይ በተደነገገው መሠረት በማድረግ ከአባላት የወለድ አልባ የብድር ፍላጎት ሲቀርብ ተጨማሪ ብድር ሊፈቀድ ይችላል፤

5. በዚህ መመሪያ አንቀፅ 21 ንዑስ-አንቀፅ 9 እና 10 መሠረት የወሰድ አልባ የብድር አገልግሎት ተጠቃሚ የብድር መክፈያ ጊዜው ሊያራዝምለት ይችላል፤
6. በሙራባሃ ብድር የተከለከሉ አሰራሮች ከዚህ በታች የተቀመጡት ይሆናሉ፤
    ሀ) በግዥና ሽያጭ አፈፃፀም ሂደት ላይ የሸሪዓ የግብይት ስርዓትን መጣስ፤
    ለ) ለንብረቱ መግዣ ዋጋ ከተመደበው ገንዘብ የተረፈውን በጥሬ ገንዘብ ለተበዳሪው መስጠት፤
    ሐ) ለግዥ ከተመደበው ገንዘብ በላይ ዋጋ ከተጠየቀ ከራሱ ገንዘብ ጨምሮ መግዛት፤
    መ) በማንኛውም ሁኔታ ጥሬ ገንዘብን በሙራባሃ ብድር ለተበዳሪው መስጠት፤
    ሠ) ለተበዳሪ የተገዛ ንብረት ገቢና ወጪ ሳይደረግ ርክክብ መፈፀም፣

37) **የሰለም ብድር አገልግሎት አሰጣጥ ስርዓት**

1. የሰለም ብድር አገልግሎት ለመስጠት የቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበር ከዚህ በታች የተዘረዘሩ አሰራሮችን መከተል አለበት፤
    ሀ) የገበያ ዳሰሳ ጥናት በማካሄድ፤
    ለ) የቀጣይ የምርት ዘመን የምርቱን ዋጋ መተንበይ እና መተመን፤
    ሐ) ተበዳሪው የሚያቀርበውን ምርት ናሙና ማቅረብ፣
    መ) በስምምነቱ መሰረት ኅብረት ሥራ ማህበሩ ለተበዳሪው ጥሬ ገንዘብ የመክፈል፣
    ሠ) በብድር አጠቃቀም ላይ ክትትል ማድረግ እና የተበዳሪውን የአመራረት ሂደት መከታተል፤
2. በዚህ መመሪያ አንቀጽ 15 ንዑስ-አንቀፅ 3 ከሀ-ሠ እና በኅብረት ሥራ ማህበሩ የብድር አሰራር ስርዓት ላይ የተጠቀሱት የብድር መገምገሚያ መስፈርቶች እንደተጠበቁ ሆነው ለሰለም ብድር አገልግሎት የሚከተሉት መስፈርቶች በተጨማሪነት ማየት አለበት፤
    ሀ) የተበዳሪው የማምረት አቅም እና የሚያመርተው ምርት ዓይነት፤
    ለ) ያለው የመሬት ስፋት፤
    ሐ) የግብዓት አጠቃቀም፤
    መ) የምርት እንክብካቤ፣ አጠባበቅ እና አሰባሰብ ልምድ፤
3. የሰለም ብድር ውል ስምምነት ሰነድ ከዚህ የሚከተሉ ጉዳዮችን ማካተት አለበት፤
    ሀ) የምርቱ ዓይነት፤
    ለ) የምርቱ መጠን በኪ/ግራም፤
    ሐ) የምርቱ የጥራት ደረጃ፤

መ) ምርቱ የተገዛበት የአንዱ ዋጋ እና ጠቅላላ ዋጋ፤

ሠ) የማስረከቢያ ቀን፣ወር እና ዓመተ-ምህረት፤

ረ) የመረከቢያ ቦታ፤

4. በሰለም ብድር አገልግሎት አሰራር ተበዳሪው በተፈጥሮ አደጋ ምክንያት የማምረት ሂደቱ መስተጓጎሉ ወይም ምርቱ መበላሸቱ በጥናት ሲረጋገጥ እና በኅብረት ሥራ ማህበሩ ሲታመን ተበዳሪው የወሰደውን ብድር በሚቀጥለው የምርት ዘመን እንዲመለስ ሊፈቀድ ይችላል፤

5. በሰለም ብድር የተከለከሉ አሰራሮች ከዚህ በታች የተቀመጡት ናቸው፤

ሀ) በውል ስምምነቱ ከተጠቀሰው የምርት ዓይነት፣ መጠን እና ጥራት ውጪ ሌላ ምርት ማስረከብ፤

ለ) ተበዳሪው የሰለም ብድርን በጥሬ ገንዘብ መመለስ፤

ሐ) ኅብረት ሥራ ማህበሩ በሰለም ብድር የሚሰበሰብ ምርት ሳይረከብ ከሦስተኛ ወገን ጋር የሽያጭ ውል መግባት

6. የሰለም ብድር አመላለስ ከዚህ በታች በተቀመጠው አሰራር መሰረት ተፈጻሚ መሆን አለበት፤

ሀ) የቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበሩ የብድር መመለሻ ጊዜ ከመድረሱ ከ15 ቀን በፊት ለተበዳሪው በፅሁፍ ማሳወቅ አለበት፤

ለ) የኅብረት ሥራ ማህበሩ በውሉ መሠረት በዕለት፣ በተቀመጠው የምርት ናሙና እና መጠን በማረጋገጥ ምርቱን ከተበዳሪው የመረከብ፤

ሐ) ኅብረት ሥራ ማህበሩ የተረከበውን ምርት መሸጥ፤

መ)ተበዳሪው ምርቱን በውል ስምምነቱ መሰረት ማቅረብ ካልቻለ በዋስትና የተያዘውን ንብረት የኅብረት ሥራ ማኅበሩ በመሸጥ ዕዳውን ማቻቻል፤

38) የኢጃራ ብድር አገልግሎት አሰጣጥ ስርዓት

1. የኢጃራ ብድር አገልግሎት ለመስጠት የቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበሩ ከዚህ በታች የተዘረዘሩ አሰራሮችን መተግበር አለበት፤

ሀ) የአዋጭነት ጥናት ማካሄድ፤

ለ) ከተካሄደው ጥናት አንጻር የተጠየቀው ምርት ወይም ዕቃ ላይ ማሻሻያ እንደምያስፈልገው ከተረጋገጠ፤ የብድር ጥያቄው ላይ ማሻሻያ ማድረግ፤

ሐ) ተበዳሪው የንብረቱን ዋጋ እና የኪራይ ክፍያ ለመክፈል መስማማት አለበት፤

መ) ተበዳሪው ንብረቱን ከተከራየ ጊዜ ጀምሮ በንብረቱ ላይ ለሚደርስ ማንኛውም ጉዳት ኃላፊነት መውሰድ አለበት፤

ሠ) የኢጃራ ብድር ውል ስምምነት መፈፀም አለበት፤

2. ሌሎች የውል ሰነድ የሚይዛቸው ይዘቶች እንደተጠበቁ ሆነው በተጨማሪ የኢጃራ ብድር ውል ስምምነት ሰነድ ይዘት ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን ማካተት አለበት፤

ሀ) የንብረቱን ዋጋ፤

ለ) የኪራይ መጠን፤

ሐ) ኪራይ የሚጀመርበትና የሚጠናቀቅበት ጊዜ የመሳሰሉትን ማካተት አለበት፤

3. የኢጃራ ብድር አመላለስ ከዚህ በታች በተቀመጠው አሰራር መሰረት ተፈጻሚ መሆን አለበት፤

ሀ) የኪራይ ክፍያ ጊዜው ታሳቢ መሆን የሚጀምረው ተበዳሪው ንብረቱን መጠቀም ከጀመረበት ቀን ጀምሮ ይሆናል፤

ለ) ተበዳሪው የተከራየውን ንብረት ዋጋ እና የኪራይ ክፍያ በውል ስምምነቱ መሰረት መክፈል አለበት፤

ሐ) ኅብረት ሥራ ማህበሩ የብድር አመላለስ ላይ ክትትል ማድረግ አለበት፤

መ) ተበዳሪው የንብረቱን ዋጋ ከፍሎ ሲያጠናቂቅ የንብረቱ ባለቤትነት ከኅብረት ሥራ ማህበሩ ወደ ተበዳሪው መተላለፍ አለበት፡፡

ሠ) ተበዳሪው የተከራየውን ንብረት ዋጋ እና የኪራይ ክፍያ በውል ስምምነቱ መሰረት ካልመለሰ ኅብረት ሥራ ማህበሩ ቅጣት ሊያስከፍል ይችላል፤

4. በኢጃራ ብድር ከዚህ በታች የተዘረዘሩ አሰራሮች የተከለከሉ ናቸው፤

ሀ) ከተደረገው የውል ስምምነት ውጪ የንብረቱ ዋጋ እና የኪራይ ክፍያ ላይ ኅብረት ሥራ ማህበሩ ምንም ዓይነት ጭማሪ ማድረግ፤

ለ) ኅብረት ሥራ ማህበሩ ንብረቱን ለኪራይ አገልግሎት ብቻ ለማዋል የውል ስምምነት ማድረግ፤

ሐ) በኅብረት ሥራ ማህበሩ ችግር ምክንያት ተበዳሪው ንብረቱን መጠቀም ሳይጀምር የኪራይ ክፍያ ማስከፈል፤

መ) በሸሪዓ ተቀባይነት የሌለውን ንብረት ማከራየት፤

ሠ) ለፍጆታ የሚውሉ ዕቃዎች ወይም ንብረቶችን ለኪራይ አገልግሎት ማዋል፣

39) የሙሻረካ ብድር አገልግሎት አሰጣጥ ስርዓት

1. ማንኛውም የቁጠባና ብድር የኅብረት ሥራ ማህበር የሙሻረካ የብድር አገልግሎት ለአባላት መስጠት ይችላሉ፤
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 መሰረት የሙሻረካ ብድር አገልግሎት ለመስጠት ከዚህ በታች የተዘረዘሩ አሰራሮችን መተግበር አለበት፤
   ሀ) የውል ስምምነቱ በገንዘብ ቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበራት ዩኒዬን እና በመሰረታዊ የቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበር መካከል ወይም በመሰረታዊ የቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበር እና በግለሰብ አባል መካከል ማድረግ፤
   ለ) የሙሻረካ ብድር ስምምነት ያደረጉ አካላት በውል ስምምነታቸው መሰረት ትርፍ እና ኪሳራቸውን መጋራት፤
   ሐ) የቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበራት እና ግለሰብ አባላት የየራሳቸውን ወጪ ታሳቢ በማድረግ የትርፍ ድርሻቸውን በፍትሃዊነት በመቶኛ መወሰን፣
   መ) የሽርክና ስራውን የማስተዳደር ኃላፊነት ለአባሉ መስጠት፣
3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 መሰረት በገንዘብ ቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበራት ዩኒዬን እና በመሰረታዊ የቁጠባና ብድር የኅብረት ሥራ ማህበራት መካከል በሚደረገው የሙሻረካ ብድር ስምምነት መሠረት የሚገኘው የትርፍ ድርሻ ከዚህ በታች በተቀመጠው መሠረት ሊሆን ይችላል፤
   ሀ) መሰረታዊ የቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበሩ የወሰደውን ብድር ለሙራባሃ የብድር አገልግሎት የሚያውለው ከሆነ ለትርፍ ህዳግ ከወሰነው መቶኛ ላይ በመጋራት፤
   ለ) መሰረታዊ የቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበሩ የወሰደውን ብድር ለሰለም የብድር አገልግሎት የሚያውለው ከሆነ ከምርት ሽያጭ ትርፍ ላይ መጋራት፤
   ሐ) መሰረታዊ የቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበሩ የወሰደውን ብድር ለኢጃራ የብድር አገልግሎት የሚያውለው ከሆነ ከኪራይ ገቢ ላይ በመጋራት፤
4. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 መሰረት ስምምነት ያደረጉ አካላት ኪሳራ በሚያጋጥማቸው ጊዜ በብድር ገንዘቡ ላይ ባላቸው የድርሻ ምጣኔ መሰረት ኪሳራውን መጋራት አለባቸው፤
5. በንግድ እንቅስቃሴው ወቅት በትርፉ ወይም በኪሳራው መጠን ላይ አለመግባባት ከተፈጠረ ትክክለኛ ማስረጃ ያቀረበ አካል ተቀባይነት ያገኛል፡፡

6. የሙሻረካ ስምምነት በመሰረታዊ የቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበር እና በግለሰብ አባል መካከል ሲደረግ ከዚህ በታች የተቀመጡ አሰራሮችን መከተል አለባቸው፤
   ሀ) ስምምነቱ ባለቤትነቱ እየቀነሰ የሚሄድ የሙሻረካ ስምምነት መሆን አለበት፤
   ለ) በሙሻረካ በሽርክና የሚከናወነው የንግድ ስራ ላይ ያላቸው የካፒታል ድርሻ በግልፅ መታወቅ አለበት፤
   ሐ) የሽርክና ንግድ ስራውን የማስተዳደር ኃላፊነት ለአባሉ መሰጠት አለበት፤
   መ) አባሉ ለንግድ ስራው አስፈላጊ የሆኑ ቅድመ-ሁኔታዎችን እና ግዴታዎችን አስቀድሞ ማሟላት አለበት፤
   ሠ) አባሉ የገቢና ወጪ መዝገብ የመያዝ ግዴታ አለበት፤
   ረ) ትርፍና ኪሳራቸውን የሚካፈሉበትን ጊዜ ገደብ በውል ስምምነት ውስጥ ማስቀመጥ አለባቸው፤
   ሰ) የኅብረት ሥራ ማህበሩ በሽርክና የንግድ ስራው ላይ ያለው ባለቤትነት የሚቆየው አባሉ የኅብረት ሥራ ማህበሩን የካፒታል ድርሻ ሙሉ በሙሉ ከፍሎ እስከሚጨርስ ድረስ ብቻ መሆን አለበት፤
7. ከዚህ በታች የተዘረዘሩት ጉዳዮች በሙሻረካ ውል ስምምነት ለብድር የሚሆን የካፒታል ድርሻ ለመወሰን ሊያገለግሉ ይችላሉ፣
   ሀ) የአባሉ መደበኛ ቁጠባ ወይም የፍላጎት ቁጠባ ወይም ሌላ ተጨማሪ ገንዘብ፣
   ለ) በገንዘብ ቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበሩ ውሳኔ መሠረት ብድር ጣሪያ ለመወሰን የሚውል የቁጠባ መጠን፤

40) የተካፉል ተአውኒ አነስተኛ የኢንሹራንስ አገልግሎት አሰጣጥ ስርዓት

1. ማንኛውም ወለድ አልባ የፋይናንስ አገልግሎትን የሚሰጥ የቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበር የተካፉል ተአውኒ አነስተኛ የመድን ዋስትና አገልግሎት—መስጠት ይችላል፤
2. ከላይ በንዑስ አንቀጽ 1 የተጠቀሰውን አገልግሎት ለመስጠት በጥናት ላይ ተመስርቶ የተካፉል ተአውኒ አነስተኛ የመድን ዋስትና የአሰራርር ስርዓት ላይ ማካተት አለበት፤
3. የተካፉል ተአውኒ አነስተኛ የመድን ዋስትና አገልግሎትን ትርፍ ለማግኘት ተብሎ የሚሰጥ አገልግሎት መሆን የለበትም፡፡

4. የተካፋል ተአውኒ አነስተኛ የመድን ዋስትና አገልግሎትን ተጠቃሚ ለመሆን ማንኛውም አባል የሚከተሉትን ቅድመ-ሁኔታዎች ማሟላት አለበት፤
   ሀ) የወለድ አልባ የፋይናንስ አገልግሎት ተጠቃሚ መሆን፣
   ለ) መተባበርን እና ልገሳን መሠረት አድርጎ ሌሎች ሰዎችን ለመርዳት የሚል አስተሳሰብ መያዝ፤
   ሐ) የተወሰነውን አረቦን ወይም ተባሩ መክፈል፣
5. የአረቦን ወይም ተባሩ መጠን የሚወሰነው ለሚደርሰው ጉዳት የሚከፍለውን ገንዘብ እና የአስተዳደራዊ ወጪን መሸፈን እንዲችል ተደርጎ መሆን አለበት፤
6. የአረቦን ወይም ተባሩ መጠን የሚወሰነው በመቶኛ ወይም በመጠን ሊሆን ይችላል፤
7. በገንዘብ ቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበሩ የተሰበሰበውን አረቦን ወይም ተባሩ የአባልን ጉዳት ለመካስ ወይም ኪሳራን ለመሸፈን መሆን አለበት፤
8. የቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበሩ ጉዳት ወይም ኪሳራ ለደረሰበት ሰው ካሳ ከመከፈሉ በፊት ጉዳቱ ወይም ኪሳራው ያደረሰው አሉታዊ ተፅዕኖ በሸሪዓ አማካሪ ቦርድ ምክረ-ሀሳብ ከተሰጠ በኋላ በኅብረት ሥራ ማህበሩ የሚወሰን ይሆናል፤
9. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 8 መሰረት የቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበሩ ጉዳት ወይም ኪሳራ ለደረሰበት ሰው ፍትሃዊ የካሳ ክፍያ መፈፀም አለበት፤
10. የቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበር ከካሳ ክፍያ የተረፈ ገንዘብን ለአባላት ትርፍ ክፍፍል የማይውል ሆኖ ለመጠባበቂያ እና ለማህበራዊ አገልግሎትም በሚኖር ምጣኔ መሰረት ይደለደላል፤

41) የወለድ አልባ የፋይናንስ አገልግሎት ሂሳብና መረጃ አያያዝ ስርዓት

1. ማንኛውም የቁጠባና ብድር የኅብረት ሥራ ማህበር የወለድ አልባ የፋይናንስ አገልግሎትን ከሌላው በመለየት ራሱን አስችሎ ለብቻ በመመዝገብ የትርፍና ኪሳራ መግለጫ ሪፖርቱን ለብቻ ማዘጋጀት አለበት፤
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 እንደተጠበቀ ሆኖ ማንኛውም የቁጠባና ብድር የኅብረት ሥራ ማህበር የሀብትና ዕዳ መግለጫ ሪፖርቱን ግልፅ በሆነ አቀማመጥ ሁሉንም አጠቃሎ በአንድ ላይ ማስቀመጥ አለበት፤
3. ማንኛውም የቁጠባና ብድር የኅብረት ሥራ ማህበር የወለድ አልባ የፋይናንስ አገልግሎት ላይ የተከናወኑ ተግባራት መረጃዎችን በአግባቡ በመሰብሰብ፣ በማደራጀት እና በመተንተን በወቅቱ አግባብ ላለው ባለስልጣን ሪፖርት ማድረግ አለበት።

ክፍል ስድስት

ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

42) የተሻሩና ተፈጻሚነት ስለማይኖራቸው መመሪያዎች

1. የቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበር የብድር አስተዳደር መመሪያ ቁጥር 008/1997 በዚህ መመሪያ ተሽሯል፤
2. ይህንን መመሪያ የሚጻረር እና የሚቃረን መመሪያ፣ ልማዳዊ አሰራር እና በመተዳደሪያ ደንብ የተቀመጠ ድንጋጌ እና ውስጠ ደንብ ውስጥ የተቀመጠ አንቀጽ ተፈጻሚነት አይኖረውም፣

43) የመተባበር ግዴታ

ማንኛዉም ሰው ይህንን መመሪያ ለማስፈጸም የመተባበር ግዴታ አለበት፡፡

44) መመሪያው የሚፀናበት ጊዜ

ይህ መመሪያ በኢፌድሪ የፍትህ ሚኒስቴር ተመዝግቦ በድረ-ገጽ ላይ ከተጫነበት ቀን ጀምሮ ተፈፃሚነት ይኖረዋል፡፡

ጌታቸው መለሰ በላይ (ፒኤችዲ)

ኮሚሽነር

አዲስ አበባ ጥር/2016 ዓ.ም

የኢትዮጵያ ኅብረት ሥራ ኮሚሽን ኮሚሽነር